
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3576 | ቅዳሜ ግንቦት 29 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# “በጤናው ዘርፍ የኢትዮጵያን የዕድገት ተምሳሌትነት እያበሰርን ነው”

## የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ

3




ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ አዳነች አቤቤ የፎሬንሲክና ስነ ምረዛ ምርመራ የልህቀት ማዕከል መርቀው ወደ አገልግሎት አስገብተዋል

## ወቅታዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

8

## ከተፈጥሮ ጋር የተወዳጁ መስህቦች

11



ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባ ከተፈጥሮና አካባቢ ጋር የተስማሙ የመስህብ ስፍራዎችን እየገነባች ነው

## የአረንጓዴው ልማት ስፖርታዊ ገጽታ

19



ፎቶ- ከገፀ ድር
ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድሐኒዓለም በተሰራው የወንዝ ዳርቻ ልማት የ‘እግር ቴኒስ’ን ጨምሮ በርካታ የስፖርታዊ እንቅስቃሴ መከወኛ ስፍራዎች ተዘጋጅተዋል

# የኢትዮጵያውያን ስልጡንነት የተገለጠበት ምርጫ

- ሕዝቡ በምርጫው ያሳየው የነቃ ተሳትፎ በአካባቢው ሀገራት ዘንድ “እኛም እንደ ኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥታችንን በዴሞክራሲያዊ አግባብ ማፅናት አለብን” የሚል መነቃቃትን የሚፈጥር ነው

**በመለሰ ተሰጋ**

ምስራቅ አፍሪካ በዓለም ላይ ካሉት እጅግ በጣም ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ካላቸው አካባቢዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ክልል ብዙ የተፈጥሮ ሀብቶችን፣ ወጣት እና እያደገ የመጣ የሕዝብ ቁጥርን፣ ዋና ዋና የባህር መዳረሻ መስመሮችን፣ ሰፊ ለም መሬት እና ከፍተኛ የታዳሽ ኃይል አቅምን የተጎናፀፈ ነው፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ- ከፋይል
ኢትዮጵያውያን 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ በተሳካ ሁኔታ አካሂደዋል

# እንጆሪ የሚቆረጥበት መንፈስ የሚታደስበት ስፋራ

- በእንጦጦ-ቀጨኔ የወንዝ ዳርቻ የለማውን የእንጆሪ ምርት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሰራ ነው

**በስንታየሁ ምትኩ**


ከእንጦጦ ተራራ ሰንሰለት እየፈለቁ አዲስ አበባን አቋርጠው የሚፈሱት ወንዞች፤ ለዘመናት ቆሻሻና ብክለት መታወቂያቸው ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተራራውና በግርጌው ባሉ የወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ የተሰሩት ከእንጨት፣ ከጭቃና ከቆርቆሮ የተሰሩ ያረጁ፣ ዕርስ በዕርስ የተዛዘሉ ቤቶችም ለስም እንጂ ለዘመናዊ የከተማ አኗኗር ፈጽሞ የማይመቹ ነበሩ፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል




**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ህዝብ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ለሰላማዊ አማራጭ ያሳየውን መሻት በስራ ማስመስከር ይገባል!

የኢትዮጵያ ህዝብ የረጅም ዘመናት የሀገረ-መንግስት ልምምድ ያላት ሀገር ባለቤት እንደመሆኑ፣ ላለፉት ዘመናት የተጓዘበትን መንገድ ትርፍና ኪሳራ በአንክሮ የመረመረ ታላቅ ህዝብ ነው። አሁን ላይ ቆመን ወደ ኋላ ስንመለከት፣ ያሳለፍናቸው የታሪክ ውጣ ውረዶች የጠቆሙን አንድ መሠረታዊ እውነት አለ። ይኸውም የሀገራችንን የወደፊት እጣ ፈንታ በሰላማዊ መንገድ ብቻ መወሰን እንደሚገባ ነው። ዛሬ የምናየው የህዝብ ተሳትፎ፣ በተለይም በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል እያደረጉት ያለው ተሳትፎና ሰሞኑን በተካሄደው ሰባተኛው ጠቅላላ ምርጫ የታየው ድንቅ የህዝብ ተሳትፎ፣ ይህንን ጽኑ አቋም በማያሻማ መልኩ ያረጋገጠ ታሪካዊ ክንውን ነው። የኢትዮጵያውያን የዛሬው ምርጫ፣ ግጭት ሳይሆን ሰላም፣ መለያየት ሳይሆን አንድነት የሚቀድምበት የዴሞክራሲ መንገድ ዋነኛና ፅኑ አላማቸው መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ሰባተኛው ጠቅላላ ምርጫ ኢትዮጵያውያን በቅድመ ምርጫው፣ በምርጫው ዕለት እና በድህረ ምርጫ ወቅቶች ያሳዩት ጨዋነትና በሳል እርምጃ የዴሞክራሲያዊ ስርአቱን ጥንካሬ ያመላከተ ነው። ይህ አካሄድ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ወደ ህዝብ አገልጋይነት የሚመጣበትን ስርዓት የመረጡበት እና ለዚያም በተግባር መወጣት ያለባቸውን ኃላፊነት በከፍተኛ ዲሲፕሊን የከወኑበት ሂደት ነው። አስቀድመው የምርጫ ካርዳቸውን በወቅቱ የወሰዱ ዜጎች፣ በምርጫ ዕለት ከሌሊት ጀምሮ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች በማቅናት፣ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ፍጹም ጨዋነት በተሞላበት መልኩ ድምጻቸውን “ሀገር ቢመራ ይበጃል” ለሚሉት መስጠታቸው፣ ለሀገራቸው ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር የሚያሳይ ነው። ይህ የዜጎች ተሳትፎ ለዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ እጅግ ወሳኝ ምሰሶ ነው።

ከዚህ በመነሳትም በምርጫው የተሳተፉ ፓርቲዎችና የግል ተፎካካሪዎች፣ የህዝብን ድምጽ የመጠበቅና የማክበር ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው። የምርጫ ውጤቱን ይፋ የማድረግ ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው አካል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሲሆን፣ ውጤቱ ይፋ ሲደረግ በጸጋ መቀበል ከሁሉም የፖለቲካው ተዋናዮች የሚጠበቅ የዴሞክራሲያዊ ስነ-ምግባር መገለጫ ነው። የፓርቲዎች የህዝብን ድምጽ በማክበር የራሳቸውን አሻራ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው ላይ ማኖር ይጠበቅባቸዋል።

መንግስት ለመመስረት የሚያስችል የህዝብ ይሁንታን የሚያገኝ ፓርቲም ቢሆን፣ ህዝቡ ያሳየውን ቁርጠኝነትና ቀናኢነት በልኩ በመረዳት ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። ህዝብንና ሀገርን በታማኝነትና በቅንነት ለማገልገል ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል። የህዝብ ድምፅ ለልማት፣ ለፍትህ፣ ለሰላምና ለጋራ ብልጽግና መዋል ያለበት ታላቅ አደራ ነው። በምርጫው ወቅት ህዝቡ የጣለውን እምነት፣ በአገልግሎትና በመልካም አስተዳደር መመለስ የዘመኑ የፖለቲካ አመራር ዋነኛ ፈተናና መለኪያ ይሆናል።

ሰባተኛው ጠቅላላ ምርጫ ለሀገር ዘላቂ ሰላምና እድገት ወሳኝ ምዕራፍ ነው። የምርጫው ስኬታማነት የሚለካው በሂደቱ ሰላማዊነትና በውጤቱ የህዝብ ድምጽ መከበር ነው። ሁሉም ዜጋ፣ የፖለቲካ ፓርቲና መንግስት የየራሱን ኃላፊነት በመወጣት፣ ለሀገር ብልጽግና የሚታገልበትን ታሪካዊ አጋጣሚ መጠቀም ይኖርበታል። ኢትዮጵያውያን በሰላማዊ መንገድ ድምጻቸውን ሰጥተዋል፤ አሁን የሚጠበቀው ይህንን ውሳኔ ማክበርና ወደ ልማት ሥራዎች መግባት ነው። የሀገር ሰላምና እድገት የሚረጋገጠው በጋራ መግባባትና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ነው። ኢትዮጵያ በህዝብ ድምጽና በሰላማዊ መንገድ የምትገነባ ታላቅ ሀገር ናትና፣ ይህንን ጉዞ በጋራ እንንከባከብ!

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## የዲጂታሉ ዘመን ማዕበል እና የትውልድ ያለማስተዋል አደጋ

**በቸርነት ዋለልኝ ከአራብሳ**

በአሁኑ ዘመን ኢንተርኔት የሰው ልጅን የዕለት ተዕለት ሕይወትና ሥልጣኔ ከቀየሩ ታላላቅ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል ግንባር ቀደሙን ሥፍራ ይይዛል። ይህንን ዓለምን በአንድ መንደር ያስተሳሰረ መረብ በአግባቡና በዕውቀት ከተጠቀምንበት ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ትምህርታዊ ጥቅሞች እንዳሉት አያከራክርም። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ይህ ቴክኖሎጂ ጥቅሙ ጎልቶ ከመታየት ይልቅ፣ አንዳንዶች ለአልባሌና ፍሬ-ቢስ ድርጊቶች የሚያውሉት መሣሪያ እየሆነ መጥቷል። ይህ ሚዛኑን የሳተ አጠቃቀም በትውልዱ የአስተሳሰብ አድማስና ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ የከፋ ጉዳት ይዞ እንዳይመጣ ከወዲሁ ሊሰራ ይገባል እላለሁ፡፡

ከዚሁ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋራ ተያይዞ እየታየ ያለው ትልቁ ቀውስ በትውልዱ የንባብ ባህል ላይ የተደቀነው አደጋ ነው። ወጣቱ ረዥም ሰዓታትን በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚለቀቁ አጫጭር ምስሎችንና የማያሰለቹ አጫጭር ጽሑፎችን በማየት ያሳልፋል። ይህ ልማድ በጥልቀት የማንበብ ትዕግሥታቸውን በማጥፋት፣ የዳበረውን የንባብ ባህላቸውን እያደከመው እንደሚገኝ ጥናቶች ያመላክታሉ። ጥልቅ ንባብ በጠፋበት ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ በሳልና በቂ ዕውቀት የጨበጠ ዜጋን ማፍራት በፍጹም የማይታሰብ መሆኑ ግልጽ ነው።

ይህ የአጫጭር መልዕክቶች ጥገኝነት ትውልዱን ከተጠቃሚነት ባለፈ፣ ሰፋና ጠለቅ ያሉ ምርምሮችን የማድረግ ዕድሉንና አቅሙን ቀምቶታል። ሳይንሳዊና ማኅበራዊ ምርምሮች ከፍተኛ ትኩረትን፣ ትዕግሥትንና ረዥም ጊዜን የሚጠይቁ ተግባራት ቢሆኑም፣ በዲጂታሉ ዓለም ፈጣን እርካታ የለመደው አእምሮ ለእንደዚህ ዓይነት አድካሚ ግን መሠረታዊ ለሆኑ ምርምሮች የመገዛት ፍላጎቱ አናሳ እየሆነ መጥቷል። ይህም ሀገራዊ ችግሮችን በጥናትና ምርምር ለመፍታት የሚደረገውን ጉዞ በእጅጉ ያደናቅፈዋል።

ሌላውና እጅግ አሳሳቢው ጉዳይ፣ ይህ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በትውልዱ ላይ የማመዛዘን ጥበብ ማጉደሉ ነው። ወጣቱ በየደቂቃው በሚለቀቁ ሀሰተኛ ወሬዎችና የተዛቡ ትረካዎች በቀላሉ የሚታለል፣ መረጃዎችን መርምሮ እውነቱን ከሐሰቱ የመለየት ብስለት የጎደለው እየሆነ መጥቷል። ነገሮችን ከስሜታዊነት በራቀ መልኩ፣ በምክንያታዊነትና በሂሳዊ አስተሳሰብ የመመዘን አቅሙ እየመነመነ መምጣቱ፣ ለማኅበራዊ ቀውሶችና ፖለቲካዊ ውዝግቦች በቀላሉ ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል።

ይህ አካሄድ በተራዘመ ጊዜ ውስጥ በትውልዱ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ የሀገርን ህልውና ክፉኛ የሚጎዳ ነው። ነገ ሀገር የሚረከበው ኃይል በጥልቀት የማያስብ፣ በዕውቀት ያልዳበረና በወሬ የሚነዳ ከሆነ፣ የማኅበረሰቡን ስብራት መጠገንና ሀገራዊ ዕድገትን ማስቀጠል አይቻልም። በመሆኑም፣ ይህንን አደገኛ አዝማሚያ በጊዜ መግታትና ችግሩን ካሁኑ መፍታት ለነገ የማይባል የቤት ሥራችን ሊሆን ይገባል። ትውልዱን ከዚህ የዲጂታል አዘቅት ውስጥ አውጥቶ ወደ መስመር ማስገባት የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ይህንን ታላቅ ሀገራዊ ስጋት ለመቀልበስ የሁሉም አካላት የጋራ ጥረትና የተቀናጀ ርብርብ የግድ ያስፈልጋል። መንግሥት የዲጂታል ደኅንነትና የአጠቃቀም መመሪያዎችን በማውጣት፣ የትምህርት ተቋማት የሂሳዊ አስተሳሰብና የንባብ ባህልን ሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ በማካተት፣ እንዲሁም ማኅበረሰቡና ቤተሰብ በቤት ውስጥ የሚደረጉ የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞችን በቅርብ በመከታተልና በመምራት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው። አሁን ካልተነሳንና ትውልዱን ከማዕበሉ ካላዳንነው፣ የነገዋ አገር ዕጣ ፈንታ የጨለመ ይሆናል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋዬ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “በጤናው ዘርፍ የኢትዮጵያን የዕድገት ተምሳሌትነት እያበሰርን ነው”

## የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በ13ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፋውን “ዘ ወሺንግ አዌ ኦፍ ሮንግስ” (The Washing Away of Wrongs) የተሰኘውን መጽሐፍ ስንገልጥ ለፍትሕ ሥርዓት መሰረት የጣለ አንድ የወንጀል ምርመራ ታሪክ እናገኛለን። በቻይናዊው ሱንግ ዙ የተጻፈውና የመጀመሪያው በሆነው የፎረንሲክ መጽሐፍ ውስጥ በአንድ የቻይና መንደር ውስጥ የአንድን ገበሬ ገዳይ ለማወቅ የሚደረግን ክትትል የሚያትት ታሪክ ሰፍሯል፡፡ በማጭድ ተመትቶ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎ የተገኘውን ሟች ነፍሰ ገዳይ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የወንጀል መርማሪው ሱንግ ዙ ለመለየት ምንም አይነት የዓይን ምስክር ባለመገኘቱ የተለየ ዘዴ ለመጠቀም ወሰነ።

መርማሪው ሱንግ በመንደሩ የሚገኙ ወንዶች በሙሉ ማጭዳቸውን ይዘው በአንድ አደባባይ እንዲሰለፉና ማጭዶቻቸውን መሬት ላይ እንዲያስቀምጡ አዘዘ። በዓይነ ቁራኛ ሲመለከት ከቆየ በኋላ፣ በአንደኛው ማጭድ ላይ ብቻ በርካታ ዝንቦች መጥተው ሲያርፉና ሲሰበሰቡ አስተዋለ። ማጭዱ በዓይን ሲታይ ንጹህ ቢመስልም፣ ዝንቦቹ ግን በማጭዱ ላይ የቀረውን የማይታይ የደም ጠብታና ጠረን አሽትተው ነበር። ነፍሰ ገዳዩም በጥፋተኝነቱ ተሸማቅቆ ወንጀሉን አመነ። ይህ አጋጣሚ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የነፍሳት ጥናትን (Entomology) ለወንጀል ምርመራ የተጠቀመበት ጥንታዊው የፎረንሲክ ምዕራፍ ሆነ። ይህ ታሪካዊ አጋጣሚም በዓለም አቀፍ ደረጃ የፎረንሲክ ምርመራ ታሪክ መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ዘመናት ነጉደው በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን (በተለይም እ.ኤ.አ በ1890ዎቹ እና 1900ዎቹ መጀመሪያ) የጣት አሻራ፣ የባሊስቲክስ (የጥይት) ምርመራ እና የደም አይነቶች ትንተና ሲተዋወቁ የፎረንሲክ ምርመራ ዘመናዊ መልክ መያዝ ጀመረ። የፈረንሳዊው ክሪሚኖሎጂስት ኤድመንድ ሎካርድ “ማንኛውም ንክኪ የራሱን አሻራ ይተዋል” የሚለው መርህ የዘመናዊው ፎረንሲክ ምሰሶ ሆነ። በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ደግሞ ሰር አሌክ ጄፍሪስ የዲ ኤን ኤ (DNA) ምርመራን ይፋ ማድረጉ፣ ፍትሕን በማስረጃ ላይ ብቻ የተመሰረተች በማድረግ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ትልቁን አሻራ አኖረ።

መዛግብት እንደሚያስረዱት ወንጀልን በሳይንሳዊ ማስረጃ የማጋለጥ ጥበብ ወይም ‘ፎረንሲክ ሳይንስ’ የአንድ ጀንበር ክስተት አይደለም፤ ይልቁንም ለዘመናት የሰው ልጅ እውነትን ፍለጋ ያደረገው ረጅም ጉዞ ውጤት ነው። የዛሬው ዓለምም ወንጀለኞች በቴክኖሎጂ ረቅቀው የሚንቀሳቀሱበት ዘመን ነው። ይህንን ተከትሎ የጸጥታና ፍትሕ ተቋማት ካልዘመኑ ወንጀልን




ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ አዳነች አቤቤ የፎሬንሲክና ስነ ምረዛ ምርመራ የልህቀት ማዕከል መርቀው ወደ አገልግሎት አስገብተዋል

መከላከል የማይታሰብ እየሆነ መጥቷል። የፎረንሲክ ሳይንስ በዋነኝነት የወንጀል ምርመራን ከባህላዊ የግምት፣ የጥርጣሬ እና ቃልን በኃይል የማስገደድ አካሄድ አውጥቶ በማያሻማ ሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ እንዲቆም አድርጎታል የሚሉት ደግሞ የሳን ፍራንሲስኮ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ሊዮ ናቸው።

በትናንትናው ዕለትም በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ዘመናዊ የፎረንሲክ (ዲኤንኤ) እና የስነ ምረዛ ምርመራ ልሕቀት ማዕከል ተመርቆ ወደ አገልግሎት ገብቷል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዚህ ወቅት፣ “የሕዝባችንን የጤና አገልግሎት በአዲስ ከፍታ ላይ የሚያስቀምጥ አዲስ የዲኤንኤ (DNA)፣ የፎሬንሲክና ስነ ምረዛ ምርመራ የልህቀት ማዕከል መርቀን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል” ብለዋል፡፡

የልሕቀት ማዕከሉ በሳይንሳዊ መንገድ የተሟሉና ዘመኑን የዋጁ መሳሪያዎችን የያዘ ነው፡፡ አንጋፋው ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ከ116 ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ከንቲባ አዳነች አውስተው፣ ይሁን እንጂ ዘመናዊ መሳሪያዎች ያልተሟሉለት እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ የለውጡ መንግሥት ለጤናው ዘርፍ በሰጠው ትኩረትም ዘመናዊ መሳሪያዎች ተሟልተውለት የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ማድረግ ተችሏል ነው ያሉት ከንቲባዋ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት ማዕከሉ ሀገራችን የውጭ ምንዛሪ የምታጣበት እና የምርመራ ውጤት ለማግኘት በጣም ረጅም ጊዜ ይፈጅ የነበረውን ችግር የሚያስቀር የዲኤንኤ (DNA) መረጃ ማከማቻና ማነጻጸሪያ ሲስተም (CODIS) ስለመያዙ ገልፀዋል። አያይዘውም በወንጀል የተጠረጠሩ፣ ወላጅነትን ለማረጋገጥና ተመሳሳይ ምርመራዎችን በዘር መለያ (DNA Profiling) ለመለየት፣ የቤተሰብ ግንኙነትን እስከ ዘር ሐረግ መለየትና ማረጋገጥ እንዲሁም አጠራጣሪ ማንነትን ለማወቅ የሚያስችል የልህቀት ማዕከል ስለመሆኑ አስታውቀዋል።

ይህ ማዕከል የሀገሪቱን የፍትሕ ሥርዓት ምርመራን ውጤታማ በማድረግና በማዘመን፣ በሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ የወንጀል ምርመራ ለማካሄድ፣ የመብት ጥያቄዎችን ለመመለስና ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ብሔራዊ የልህቀት ማዕከል ስለመሆኑም ተገልጿል።

“ሁሌም ቃልን በተግባር ፈፅመን በቁርጠኝነትና በተሻሻለ የስራ ባህል እየሰራን ባለፉት 5 ዓመታት ለጤናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት 4 ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚመጥኑ ሆስፒታሎች በመገንባትና ነባር ሆስፒታሎችንም በማደስና በማስፋፋት ሰፊ ስራዎችን ሰርተን አዘምነናቸዋል” ብለዋል ከንቲባ አዳነች አቤቤ፡፡ አክለውም የከተማ አስተዳደሩ በጤናው ዘርፍ የኢትዮጵያን የዕድገት ተምሳሌትነት እና የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ምዕራፍ እያበሰረ ነው! ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የጤና ሚኒስትር መቅደስ ዳባ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ማዕከሉ የፎረንሲክ፣ የዘረ መልና የስነ ምረዛ አገልግሎትን በአንድ መስኮት አገልግሎት መስጠት ያስችላል ብለው፣ በዘመናዊ መንገድ የተደራጀው የልህቀት ማዕከሉ ለከተማዋ ብሎም ለሀገሪቱ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደምም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራና የምርምር ልህቀት ማዕከልን መርቀው በከፈቱበት ወቅት ባደረጉት ንግግር፤ ማዕከሉ ባለፉት ዓመታት በጸጥታ እና ደህንነት ዘርፍ የተከናወኑ የሪፎርም ስራዎች ውጤት መሆኑን ገልፀው ነበር፡፡

የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራና የምርምር ልህቀት ማዕከል ዘመኑን በዋጀ ቴክኖሎጂ የተደራጀ ሲሆን፤ የሰነድ፣ የዘረ መል (ዲኤንኤ) ዲጂታል ፎረንሲክ፤ ስውር አሻራና ሌሎች ከፎረንሲክ ጋር የተያያዙ የምርምር ስራዎች የሚከናወኑበት መሆኑን ጠቁመው፣ ማዕከሉን የመከላከያ ሰራዊት ደግሞ ከውጭ ይገቡ የነበሩ የኮሙኑኬሽን መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ በማምረት የፖሊስ ስራ ይበልጥ እንዲደራጅ እያደረገ ስለመሆኑም አንስተዋል።

ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረሚካኤል በዚሁ ወቅት፣ አገልግሎቱ የፖሊስ የምርመራ ስራን በማጎልበት ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል። ለፍትሕ ሥርዓቱ የተሻለ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ አገልግሎቱን በውጭ ሀገር ለማግኘት ታወጣው የነበረውን ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚያስቀርም አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪ አገልግሎቱ በፍርድ ቤት ለሚታዘዙ የምርመራ ስራዎች እንዲሁም ከቤተሰብ ጋር ተያይዞ ለሚቀርብ የዲኤን.ኤ ምርመራ ለመስጠት እንደሚያስችልም አብራርተዋል። በአጠቃላይ አገልግሎቱ ኢትዮጵያ በአህጉር አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ ተቋም ለመገንባት እያከነወነች ያለውን ስራ በማገዝ ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑንም ነው ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረሚካኤል የተናገሩት፡፡

ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች የሚንቀሳቀሰው የፎረንሲክ ምርመራ ማዕከል የሀገርን ኩራትና ሀብት የታደገ ትልቅ እመርታ ሆኗል። ይህ ተቋም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ሀገራትም ጭምር የሚተርፍ አቅም ይዞ ብቅ ብሏል። ኢትዮጵያ ይህንን ዘመናዊ የፎረንሲክ አገልግሎት በሀገር ውስጥ በይፋ ከመጀመሯ በፊት፣ የወንጀል ምርመራና የፍትሕ ሥርዓቷ ላይ ሰፊና አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች ነበሩባት። በተለይም ውስብስብ የሆኑ የዘረ መል (DNA) ምርመራዎችን ለማድረግ ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ትገደድ የነበረ ሲሆን፤ ይህ አሰራር ለእያንዳንዱ ናሙና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስወጣ ከመሆኑም በላይ፣ የምርመራ ውጤቱ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ወራትን አልፎ ተርፎም ዓመታትን በመውሰድ ለፍትሕ መጓተትና ለዜጎች እንግልት ዋነኛ ምክንያት ነበር። ይህ አገልግሎት በሀገር ውስጥ መሰጠቱ ይህንን ጥልቅ ክፍተት የደፈነ ትልቅ ሀገራዊ ጥቅምን አስገኝቷል። በአንድ በኩል፣ የናሙና ውጤቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማቅረብ የፍርድ መዘግየትን ያስቀረ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቶችም ሳይንሳዊ እውነት ላይ ተመስርተው ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጡ በር ከፋች ሆኗል።

# የኢትዮጵያውያን ... ከገጽ 1 የዞረ

ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ እና ኤርትራ የሚገኙበት ይህ ቀጣና ዓባይን የመሳሰሉ ታላላቅ ወንዞችን፣ እምብዛም ጥቅም ላይ ያልዋለ የነዳጅ እና የጋዝ ክምችትን፣ ወርቅ፣ ታንታለም፣ የከበሩ ድንጋዮች እና ሌሎች ማዕድናትን ተፍጥሮ ሳትሰስት ለግሳዋለች፡፡

ቀጣናው አፍሪካን፣ መካከለኛው ምስራቅን፣ የህንድ ውቅያኖስን እና ዓለም አቀፍ የመርከብ መስመሮች በሚያገናኝ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ በዓለም ላይ ካሉት በጣም አስፈላጊ የባህር ወሽመጦች መካከል አንዱ በሆነው የባብ ኤል ማንደብ አቅራቢያ በምትገኘው ጂቡቲ እና በዙሪያዋ የዓለማችን ኃያላን ሀገራት እንቁላሏን በንቃት እንደምትጠብቅ ሰጎን ዐይኖቻቸውን ብቻ ሳይሆን ጦራቸውንም ወድረው በተጠንቀቅ ቆመዋል፡፡

ለአብነትም አሜሪካ ካምፕ ሌሞኒየር እና ቻቤሊ አየር ማረፊያን፣ ቻይና የሕዝብ ነፃ አውጪ ጦር የድጋፍ ጣቢያን፣ ፈረንሳይ የፈረንሳይ የአየር ጣቢያ 188 እና የፈረንሳይ የባህር ኃይል ተቋማት፣ ጃፓን የጃፓን ራስን የመከላከል ኃይል ጣቢያ እንዲሁም የጣሊያንን የአሜዴኦ ጉሌት ወታደራዊ ድጋፍ ጣቢያ በማለት የሰየሟቸውን የጦር ሰፈሮች መጥቀስ እንችላለን፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ያህል ሀብት፣ ጅኦ ፖለቲካዊ አቀማመጥ፣ ዓለም አቀፍ ትኩረትና ተፈላጊነት ያለው ክልል በተጠና፣ ውስብስብና ታሪካዊ ሴራዎች፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ዕርስ በዕርስ ጦርነት የሚታመስ፣ በልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች ብዙ መከራዎችን እያሳለፈ ያለም አካባቢ ነው።

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በሕገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል የፖለቲካ ሳይንስና ፌዴራሊዝም ምሁር ኃይለኢየሱስ ታዬ (ዶ/ር) እንደሚሉት የአፍሪካ ቀንድ በጣም ያልተረጋጋ አካባቢ ነው፡፡ ይህም በአካባቢው የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለመፈጠሩ ነው፡፡ በፖለቲካል ሳይንስ እሳቤ መሰረት "ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ ሀገራት ዕርስ በዕርስ አይስማሙም። በመሆኑም በአካባቢው ዴሞክራሲ ባለመዳበሩ አንዱ አንዱን ለማጥፋት በሴራ ይንቀሳቀሳል፡፡"

እንደ ኢትዮጵያ ግን ባለን ጠንካራ ባህልና ታሪክ፣ ወጣትና እያደገ የሚሄድ የሕዝብ ቁጥር፣ ባለን ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ፣ ለአፍሪካ ነፃነትና ከፍታ ባደረግነው አስተዋፅኦ ልክ ሀገረ መንግሥትን አፅንቶ የማቆየት ልምምድ አለን፡፡ በ7ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሕዝቡ ያሳየው የነቃ ተሳትፎም ይህንን የሚመሰክር ነው፡፡ ከ54 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን በንቃት የተሳተፉበት ይህ ምርጫ በአካባቢው ሀገራት ዘንድ 'እኛም እንደ ኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥታችንን በዴሞክራሲ አግባብ ማፅናት አለብን' የሚል መነቃቃትንም የሚፈጥር ነው፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያውያን 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ በተሳካ ሁኔታ አካሂደዋል

በትክክልም ኢትዮጵያ በብዙ መስፈርቶች የተረጋጋች ናት፡፡ በተለይም ካለፉት ስምንት ዓመታት ወዲህ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን እያረጋገጠች፣ ሰብዓዊነትንም ከፍ እያደረገች፣ በየዘመኑ እየተንከባለሉ የመጡ ስብራቶቿን በሚጠግኑ ምክክርን የመሳሰሉ ዘመናዊ የፖለቲካ እሳቤዎችን እየተገበረች፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቋማቶቿን እያጠናከረች እና ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂና አሰራርን በመከተል በብዙ መመዘኛዎች ለአፍሪካውያን ሁለንተናዊ ተምሳሌትነቷን አስጠብቃና ከፍታዋንም ጨምራ ቀጥላለች፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ኢትዮጵያውያንን "ድንቅ እና ተዓምራዊ ሕዝብ" ሲሉ ገልጸዋቸዋል። በምርጫ ሂደቱ ውስጥ ለመሳተፍ ቀዝቃዛ ምሽቶችን፣ ረጅም ጉዞዎችን፣ ዝናብን፣ ህመምን፣ እርጅናን፣ ማህበራዊ ግዴታዎችን እና የተለያዩ ጫናዎችን የታገሉ ዜጎችን አድንቀዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለተመራጮቹ "ያከበሩህን እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ዋጋ የከፈሉትን አክብረህ ይህንን ሕዝብ በቅንነት እንድታገለግል" ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

ይበልጥም "ያከበሩህን አክብር" የሚለው ሐረግ የዴሞክራሲን መሠረታዊ መርህ ያነገበ ድንቅ አባባል ነው፡፡ መልዕክቱ ሉዓላዊ ሥልጣን የሕዝብ መሆኑን ይመሰክራል፡፡ ዜጎች በምርጫ በመሳተፍ በሀገሪቱ ተቋማት ላይ ያላቸውን እምነትንም ያሳያል፡፡ ተመራጮች ደግሞ በተራቸው ተጠያቂነት ባለው አግባብ ያመናቸውን ሕዝብ በታማኝነት ማገልገል እንዳለባቸውም ጠንከር ያለ ጥሪን ያቀርባል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስና ፌዴራሊዝም ምሁሩ ኃይለኢየሱስ ታዬ (ዶ/ር) "ያከበሩህን አክብር" በሚለው ሀሳብ ይስማማሉ፡፡ ምንም እንኳ በሀገር ውስጥ ያሉና የሰላምና ዴሞክራሲያዊ መንገድን ያልመረጡ አካላት እንዲሁም የተወሰኑ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀሩ አሉታዊ ነገሮችን ቢያራግቡም ሕዝቡ በሰለጠነና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በምርጫ ፍላጎቱን ገልጿል፡፡ "የምፈልገው ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ብቻ ነው"ም ብሏል፡፡

በመሆኑም ተመራጮች አክብሮ የመረጣቸውን ሕዝብ ከቀደመው የበለጠ ሀገር ወደፊት እንድትራመድ በመትጋት፣ በተለይም ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመስራት መብቱ እንዲጠበቅ የታችኛውን (ወረዳና ቀበሌ ላይ ያለውን) መዋቅር በልዩ ትኩረት በማጠናከር፣ ፀጥታውን እንዲያስከብር፣ ማህበረሰቡን በቅንነትና በታማኝነት እንዲያገለግል፣ መሰረታዊ ችግሩን ነቅሶ በማውጣት እና በመፍታት እንደ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎቶችን የመሳሰሉ አሰራሮችንም በሁሉም ዘርፎች በመዘርጋት ተመራጮች አክብሮ የመረጣቸውን ሕዝብ ማክበር እንደሚጠበቅባቸውም ሙያዊ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

መራጩ ኅብረተሰብም ምርጫ የአንድ ቀን ጉዳይ ብቻ አይደለምና በዴሞክራሲያዊ መንገድ በድምፁ የተከለውን ስርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሀሳብ አለን ብለው የሚንቀሳቀሱ ሁሉም አካላት እንዲቀበሉ አሁንም ግፊት ማድረግ ይጠበቅበታል። በሌላ በኩልም ከዚህ ሥርዓት ውጭ የሚሆኑ አፈንጋጮችን ደግሞ 'ዞር በሉ፤ ሀሳባችሁን ይዛችሁ በምርጫ ቅረቡ' ማለት እንዳለበትም መክረዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) "ያከበሩህን አክብር" የሚለው መልዕክት መራጩ የከፈለውን ዋጋና መሻቱንም የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተመራጮች በምትኩ ሕዝባቸውን በፍትሐዊና ቀልጣፋ አገልግሎት፣ በተጠያቂነት እና ለሕዝብ ታማኝ የመሆን የሞራል እና የፖለቲካ ግዴታ እንዳለባቸው ያመላክታል፡፡

ይህ መርህ ከዴሞክራሲያዊ ፅንሰ-ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሲሆን፣ በዚህ መስመር የተጓዙ መንግሥታት ሕዝባቸውን እና ሀገራቸውን ከፍ ባለ ማማ ላይ ማስቀመጥ ችለዋል ይላሉ በሀያኛው ክፍለ ዘመን ከፍተኛ ተደማጭነት ካላቸው የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን መካከል ፕሮፌሰር ሮበርት አለን ዳህል እ.ኤ.አ 1989 Democracy and Its Critics በተሰኘው መፅሐፋቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክትም ከላይ ያነሳነውን አንኳር ሀሳብ "የሀገራችን ፖለቲከኞችና ልሂቃን ይህንን ታላቅ ጽኑ ጨዋና ቆራጥ ሕዝብ የምንረዳውና የምንመጥነው መሆን ይጠበቅብናል" በማለት ገልፀውታል፡፡

የሀገረ መንግሥቱን ግንባታ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አቅጣጫ ውጭ ባንዳና ባዳ ጥምረት ፈጥረው በአመፅና በኃይል ሀገራችንን ወደ ጥፋት መንገድ ለመክተት ያሴሩትን ደባ ሕዝቡ በዴሞክራሲያዊው ምርጫ እምቢተኝነቱንና ለሀገር ያለውን ፅኑ ፍቅር በተግባር በማሳየት አክሽፎታል፤ ኢትዮጵያም አሸነፈች፤ ብለዋል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ እና የፌዴራሊዝም ምሁር ኃይለኢየሱስ ታዬ (ዶ/ር) በበኩላቸው ምርጫው ለኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ትልቅ መሰረት የጣለ ነው፡፡ እርሳቸውም ሕገ መንግሥታዊ የመምረጥ መብታቸውን እውን ለማድረግ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ድረስ ወረፋቸውን ጠብቀው እንደመረጡ አስታውሰው፣ በምርጫው ቀን የነበሩ ረጃጅም ሰልፎችና የሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ የሚያሳየው ሀገረ መንግሥት ማስቀጠል ብቻ ሳይሆን ሀገረ መንግሥቱ የሚቀጥልበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ መሆን እንደሚገባው ማኅበረሰቡ ፍላጎቱና አቋሙን የገለፀበትም ጭምር እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

# 7ኛው ምርጫ በመራጮች አንደበት

በቶለሳ መብራቴ

ኢትዮጵያ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ አካሂዳለች፤ በምርጫው የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት ደግሞ ድምፃቸውን የሰጡት መራጮች ናቸው። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከሌሊቱ 11:00 ሰዓት ጀምሮ፣ የምርጫ ጣቢያ በሮች ከመከፈታቸው አስቀድሞ፣ በስፍራው በመገኘት ግዴታቸውን ለመወጣት ያላቸውን ቁርጠኝነት አሳይተዋል። በዲሲፕሊን እና በትዕግስት የተሞላው የመራጮች ፅናት እስከ ሌሊት ድረስ የቀጠለ ሲሆን፣ ያሳዩት ሰላማዊ እና ጨዋነት የተሞላበት ባህሪ የትኛውንም መሰናክል በጽናት ማለፍ እንደሚችሉ በግልጽ ያሳዩበት አጋጣሚ ሆኖ አልፏል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ውሳኔ የችግሮች ሁሉ መፍትሄ የሰላማዊ መንገድ አማራጭ ብቻ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ማመናቸውን ያሳዩበት ታላቅ ታሪካዊ ምዕራፍ ነው። መራጮች በማለዳው ቅዝቃዜና በምሽቱ ድካም ሳይበገሩ፣ ድምፅ ለመስጠት ያሳዩት ቁርጠኝነት ለሀገራችን የፖለቲካ ብስለት ትልቅ እምርታ ነው።

ይህ ሂደት የኢትዮጵያ ህዝብ ከማንኛውም የኃይል አማራጭ ይልቅ በሰላማዊ ድምፅ የሚገነባ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን አጥብቆ እንደሚሻ እና ለዚህም መሳካት ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ለዓለም ህዝብ በኩራት ያበሰረበት ደማቅ አሻራ ነው። በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረን ያነጋገርናቸው ነዋሪዎችም ይህንኑ መስክረዋል፡፡

## ለሀገሬ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩሌን አሻራ ማሳረፍ የዜግነት ግዴታዬ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ክብርም ነው።



ሀና ደንበል እባላለሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነኝ። የምርጫ ካርዴን ከወሰድኩበት ጊዜ ጀምሮ ድምፄን ለመስጠት በከፍተኛ ጉጉትና ፍላጎት ነበር የጠበቅኩት። ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ መብቴን የተገበርኩበት ዕለት በመሆኑ ኩራት ይሰማኛል፡፡

ለሀገሬ ያለኝን ፍቅር ለማሳየት ከሌሊቱ 11:00 ሰዓት ነበር ከቤት ወጥቼ ወደ ምርጫ ጣቢያዬ የሄድኩት፡፡ በምርጫ ጣቢያው የነበረው ወረፋ በጣም ረጅም በመሆኑ፣ ድምፄን ሰጥቼ ለመጨረስ እስከ ቀኑ 7 ሰዓት ድረስ በትዕግስት ጠብቄያለሁ።

የመንግስት ስልጣን ሊገኝ የሚችለው በጠመንጃ ወይም በኃይል ሳይሆን፣ በሰላማዊ መንገድ በምናስቀምጠው ካርድ ብቻ መሆኑን በሚገባ አምናለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመረጠች አንዲት ወጣት፣ ለሀገሬ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩሌን አሻራ ማሳረፍ የዜግነት ግዴታዬ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ክብርም ነው። ያሳየሁት ትዕግስትም ለምመኛት የበለጸገች ሀገር የምከፍለው ትንሽ መስዋዕትነት በመሆኑ፣ በሰልፉ ላይ በነበረኝ እያንዳንዱ ደቂቃ በውስጤ የሚሰማኝ ኩራትና ደስታ ወደኋላ እንዳልል ገፋፍቶኛል።

## ከዚህ ምርጫ በኋላ የሚመጣው አስተዳደር የሕዝቡን አደራና የልማት ጉጉት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሀገራችንን የብልጽግና ጉዞ እንደሚያፈጥን፣ ተስፋ አደርጋለሁ።



ዳኛቸው ሽፈራው እባላለሁ በአዲስ አበባ ከተማ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ነኝ፡፡ ድምፅ ለመስጠት ጠዋት በማለዳ ተነስቼ ወደ ምርጫ ጣቢያዬ ሄድኩ። ለተወሰነ ጊዜም በትዕግሥት ጠብቄ ድምፄን ሰጥቻለሁ። የከፈልኩት ዋጋ ጊዜዬን፣ ጉልበቴን እና ትዕግሥቴን መስዋዕት ማድረግ ነበር።

በምርጫው እንድሳተፍ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት የሀገሬ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በዜጎች ንቁ ተሳትፎ እንደሚወሰን ያለኝ እምነት ነው። አንድ ድምፅ ትንሽ ቢመስልም ለለውጥ፣ ለሰላም እና ለተሻለ አስተዳደር መመስረት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው አምናለሁ። ስለዚህ የዜግነት ኃላፊነቴን በመወጣት ድምፄን በኩራት ሰጥቻለሁ።

ዜጎች የዕለት ተዕለት የኑሮ ጫናዎችና ተግዳሮቶች ቢኖሩም፣ በሰላማዊ መንገድ ሰልፍ ይዘው ድምፃቸውን ለመስጠት መውጣታቸው የዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ዋጋ በሚገባ ጠንቅቀው መረዳታቸውን ያሳያል። በቅሬታ ወይም በኃይል ሳይሆን፣ በካርድና በምርጫ ብቻ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ህዝቡ ያለው ጽኑ እምነት በተግባር የታየበት አጋጣሚ ነው።

ምርጫው ያለምንም መገፋፋት፣ በከፍተኛ ስነ-ስርዓትና ዕርስ በዕርስ በመከባበር መጠናቀቅ መቻሉ፣ ማህበረሰባችን ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ የሚችልበት የታላቅነትና የብስለት ደረጃ ላይ መድረሱን ያረጋግጣል።

ሰላም ባለበት ሀገር እድገት መኖሩ አይቀሬ ነው። ከዚህ ምርጫ በኋላ የሚመጣው አስተዳደር የሕዝቡን ታላቅ ትዕግስትና የልማት ጉጉት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሀገራችንን የብልጽግና ጉዞ እንደሚያፈጥን፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገታችንም ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚሸጋገር ተስፋ አደርጋለሁ።

## ይህ ምርጫ ያሳየን ትልቁ እውነት ሕዝባችን በሰላማዊ መንገድ የመጓዝ ጽኑ ውሳኔ ላይ መድረሱን ነው።



ሄኖክ ጥላሁን እባላለሁ በአዲስ አበባ ከተማ የቦሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ነኝ፡፡ በሀገራችን ውስጥ በተካሄዱት በሰባቱም አገራዊ ምርጫዎች ላይ ያለማቋረጥ ተሳትፌአለሁ። ይህንን የማደርገው እንዲሁ በዘፈቀደ ሳይሆን፣ የምርጫ ካርድ መውሰድና ድምፅ መስጠት የዜግነት ግዴታ መሆኑን በጽኑ ስለምረዳ ነው። የምሰጠው ድምፅ የነገዋን ብሩህ ሀገር ለመገንባት የምናበረክተው ውድ ስጦታ በመሆኑ፣ ይህንን ታሪካዊ አደራ በደስታና በኩራት እወጣዋለሁ።

ሰላማዊና መከባበር የተሞላበት የምርጫ ሂደት መጪው ትውልድና ልጆቻችን አይተው ሊረከቡትና ሊወርሱት የሚገባ ታላቅ አርአያነት ነው። ሀገራችንን ወደ ተሻለ የእድገትና የዴሞክራሲ ምዕራፍ የሚያሻግር ታሪካዊ መሠረት እየተጣለ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

ማልዶ በሌሊት ወጥቶ፣ ረጃጅም ሰልፎችንና የቀትር ፀሐይን በትዕግስት የተቋቋመው ያ ሁሉ መራጭ ያሳየው ፍጹም ስልጡን ጠባይ የዚሁ ማረጋገጫ ነው። ዕርስ በዕርስ በመከባበርና በመረዳዳት ሂደቱን ማከናወኑ ማህበረሰባችን ልዩነቶችን ማስተናገድ የሚችለው በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ መወሰኑን ያሳያል።

በምርጫ ጣቢያዎች የታየው ለአቅመ-ደካሞች፣ ለነፍሰ-ጡሮችና ለአረጋውያን ቅድሚያ የመስጠት መልካም ባህል ልብን በደስታ የሚሞላ ትዕይንት ነው፡፡ ይህ ምርጫ ያሳየን ትልቁ እውነት ሕዝባችን በሰላማዊ መንገድ የመጓዝ ጽኑ ውሳኔ ላይ መድረሱን ነው። ከዚህ ምርጫ በኋላ የምንመሰርተው የፖለቲካ ባህል ይበልጥ የጎለበተ፣ ልዩነቶችን በውይይትና በሕግ ማዕቀፍ የሚያስተናግድ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

## ይህ ተሳትፎዬ ለእኔ የዜግነት አሻራዬ እና የታማኝነቴ መገለጫ ነው።



አቶ ወንድሙ ሻቃ እባላለሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነኝ፡፡ እኔ በሀገራችን የምርጫ ታሪክ ውስጥ አዲስ አይደለሁም፤ እስካሁን ድረስ በተካሄዱት አገራዊ ምርጫዎች ላይ ለሰባት ጊዜያት ድምፄን ሰጥቻለሁኝ። ይህ ተሳትፎዬ ለእኔ የዘወትር የዜግነት አሻራዬ እና የታማኝነቴ መገለጫ ነው።

በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ዕለት የበኩሌን ድርሻ ለመወጣት ከቤቴ የወጣሁት ከረፋዱ አምስት ሰዓት ተኩል ላይ ነበር። ይሁን እንጂ በጣቢያው የነበረው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥርና ረጅም ሰልፍ፣ ሙሉ ሂደቱን አጠናቆ ለመምረጥ እስከ ምሽት 1 ሰዓት ድረስ በጣቢያው እንድቆይ አስገድዶኛል፡፡

ምንም እንኳን የዕድሜዬ መግፋት ይህን ሁሉ ሰዓት ለመሰለፍ ባይፈቅድልኝም፣ ለአረጋውያንና ለአቅመ-ደካሞች የተሰጠውን ልዩ ቅድሚያ ተጠቅሜ ሂደቱን ለማሳጠር አልፈለግኩም። ይልቁኑም ለሀገሬ የምከፍለውን ታሪካዊ ዋጋ በራሴ ትዕግስትና ብርታት ለመወጣት በመምረጥ፣ ያንን ረጅም ሰልፍ በጽናትና በትዕግስት ተቋቁሜ ድምፄን ሰጥቻለሁ፡፡

ፎቶ- በገነት ወንድሙ





ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ከእንጦጦ ተራራ ግርጌ የለማ የእንጆሪ ምርት እና የንብ ማነብ ሥራ በከፊል

# እንጆሪ ... ከገጽ 1 የዞረ

ሀምሳ አለቃ መለሰ ጨረፎ እድገታቸውና ኑሯቸው በተለምዶ “ቀጨኔ መቀጠያ” እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ነው፡፡ በአካባቢው ከ60 ዓመታት በላይ የኖሩት እኚህ አባት፣ ከቀጨኔ እስከ እንጦጦ ያለውን አካባቢ ጠንቅቀው ያውቁታል፤ በልጅነታቸው በወንዙ ዳር ኳስ ተጫውተው፣ በንጹህ ውሃው ዋና ዋኝተውና ቦርቀው አድገውበታል፡፡

“እኔ በልጅነቴ ሳውቀው ከቀጨኔ እስከ እንጦጦ ያለው አካባቢ በጥቅጥቅ ጫካ የተሸፈነ ነበር፤ ወንዙም እጅግ ንጹህና ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ነበር” ሲሉ የዱሮው ትዝታቸውን ያነሳሉ፡፡ ነገር ግን በአካባቢው ሰዎች መኖር ሲጀምሩና የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ሲመጣ ተፈጥሯዊ ይዘቱን እያጣ መጣ። አካባቢው በደሳሳ ቤቶች ተጨናነቀ። ከየቤቱም የሚወጡ ጥቅም ላይ የዋሉ በተለምዶ ሃይላንድ ተብለው የሚጠሩ የፕላስቲክ ውሃ መያዢያ እና ከየቤቱ የሚወጡ ቆሻሻዎች መጣያ ሆነ፡፡

ሀምሳ አለቃ መለሰ የቦረቁበት፣ በሒደት በበጋ አቧራ በክረምት ደግሞ ጭቃ የነበረው ሜዳ ዛሬ ታሪክ ሆኗል፤ በእሱ ምትክ ዘመናዊ ስታዲየም ተገንብቶ ለአካባቢው ወጣቶች አዲስ እድል ይዞ መጥቷል። የልማት ስራው ያመጣው መነቃቃት የእሳቸውንም ቤት በር አንኳኩቷል። እሳቸውም በመበረታታት፣ የነበረውን የቆርቆሮ አጥር አንስተው በድንጋይና በግንብ በማጠር፣ ቀለም በመቀባት ቤታቸውን ከአዲሱ የአካባቢው ውበት ጋር አስማምተዋል፡፡

ስለአካባቢው ማህበረሰብ ህይወት አስመልክቶ ሀምሳ አለቃ መለሰ እንደገለጹት፤ “አብዛኛው የአካባቢ ማህበረሰብ የሚተዳደረው በሽመና፣ በሽክላ ጥበብ እና ከጫካ የማገዶ እንጨት እና ቅጠል ለቅሞ በመሸጥ በአነስተኛ ገቢ ነበር” ይላሉ፡፡ ነገር ግን ለውጥ ለማምጣት አካባቢው ትኩረት አልተሰጠውም ነበር ሲሉም አያይዘው ገልጸዋል፡፡ አሁናዊ ለውጡን ሲናገሩም፤ በዚህ በልማቱ ወንዙ ንጹህና ውብ ገፅታን እንዲላበስ ከመደረጉ ባሻገር የእንጆሪ፣ ብርቱካንና የተለያዩ ፍራፍሬዎች በአካባቢያቸው ለምቶ ማየታቸው ፍጹም አዲስና ያልተለመደ ክስተት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ “ለውጡ እጅግ ያኮራል፤ እንደ እንግዳ እየመጣሁ ነው የምመለከተው!” ሲሉም በአድናቆት ይናገራሉ፡፡

ወ/ሮ ገነት በለጠም በአካባቢው ከ30 ዓመታት በላይ ኖረዋል፡፡ ቀደም ሲል ስላለው ሁኔታ ሲያስታውሱ፤ “ከአንድ ዓመትና ሁለት ዓመት በፊት አካባቢው የዘመሙ ቤቶች የሞሉበት፣ ወንዙና ዳርቻው ደግሞ የቆሻሻ መጣያና የመፀዳጃ ስፍራ ነበረ” ይላሉ። ቦታው በጥሻ የተሸፈነ፣ ወንጀለኞችና ቀማኞች የሚደበቁበት፣ ሴቶች የሚደፈሩበት፣ በአጠቃላይ የተረሳና የሚያስፈራ እንደነበረም ያነሳሉ።

ዛሬ ግን በወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክቱ አማካኝነት ያ አስፈሪ ታሪክ ተቀይሮ አካባቢው ንጹህና ውብ ስፍራ ለመሆን በቅቷል። አዳዲስ መንገዶች ተሰርተዋል፤ ዘመናዊ የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ እና የንግድ ሱቆች ተገንብተዋል። ከዚህ ቀደም በአካባቢው ያልተለመዱ አትክልትና ፍራፍሬዎችም ለምልመው ይታያሉ።

ወ/ሮ ገነት “በአካባቢያችን ለውጥ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ፅዱና ውብ መሆኑ ከተለያዩ ቦታዎች ሰዎች ወደዚህ እንዲመጡ ያደርጋል። ለልጆቻችን ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥርላቸዋል” በማለት ለውጡን አድንቀዋል።

የእንጦጦ-ቀጨኔ መድኃኒዓለም የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት፣ ወንዞችን ወደ ተፈጥሯዊ ገፅታቸውና ውበታቸው ከመመለስ ባለፈ አንድ ትልቅ እውነት በተግባር አሳይቷል፡፡ ወንዞች የውበትና የመዝናኛ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ የከተማ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ አቅም እንዳላቸው ነው፡፡

ከእንጦጦ ግርጌ ባለው የወንዝ ዳርቻ በሚገኝ ቦታ ላይ ለምተው ለምርት ከደረሱ ፍራፍሬዎች መካከል እንጆሪ አንዱ ነው። በአሁኑ ወቅት በመንግስትና የግል አጋርነት በተቋቋመው የ“እንጦጦ የወንዝ ዳርቻ እርሻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር” የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ የሆኑት አቶ ነቢል በሻህ እንደገለጹት፤ የእንጆሪ ፍራፍሬው የለማበት አካባቢ ቀደም ሲል የተፋፈጉና ያረጁ፣ ከእንጨት፣ ከጭቃና ከቆርቆሮ የተሰሩ ለኑሮ የማይመቹ እንዲሁም ለእይታ የማይማርኩ መኖሪያ ቤቶች የነበሩበት ነበር፡፡ በተጨማሪም ወንዙ ከመኖሪያ ቤቶች በሚወጡ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻዎች ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ የተበከለ ነበር፡፡

በአዲስ አበባ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለስልጣን የፕሮጀክት አፈፃፀም ክትትል ባለሙያ አቶ መታሰቢያ አየለ ይህንን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡ አካባቢው ትናንት “ከደረጃ በታች” የሆኑ የተጠጋጉ ቤቶች፣ መንገድና መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው ቤቶች፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎች የተበራከቱበት፣ ለአይን የማይማርክ፣ የወንጀለኞችና የቀማኞች መደበቂያ በመሆን ለነዋሪዎች ስጋት ሆኖ ነበር፡፡

ማህበረሰቡን በፕሮጀክቱ ፋይዳ ላይ በማሳመንና ምትክ ቦታ በመስጠት፣ ወንዙን በማፅዳትና “የወንዝ ዳርቻው ለምን ዓይነት የከተማ ግብርና ልማት ሊሆን ይችላል?” በሚል ጥናት በማካሄድ በአካባቢው ባልተለመደ መልኩ የእንጆሪ ምርት እንዲለማ በማድረግ ለምርት ማድረስ ተችሏል፡፡ በወንዝ ዳርቻው ወደ 15 ሄክታር ስፋት ባለው የአረንጓዴ ልማት አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የንብ ማነብ ስራዎች በስፋት እየተከናወኑበት እንደሚገኝ አቶ መታሰቢያ ያነሳሉ፡፡

ይህም መንግስት የከተማ ግብርና እና የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብርን በመንደፍ በምግብ ራስን የመቻል፣ የስራ ዕድል ፈጠራንና ገቢን የማሳደግ ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም እንደሆነ አቶ መታሰቢያ ያነሳሉ፡፡ “ከዚህ ቀደም ጫካዎችና የወንዝ ዳርቻዎች ለአካባቢ ጥበቃ ጥቅም በሌለው ባህር ዛፍና በጥሻ የተሸፈኑ ነበሩ። አሁን ግን እንደ እንጆሪ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ አቮካዶ ያሉ የፍራፍሬና የተለያየ የመድኃኒትነት ጠቀሜታ ባላቸው ዕፅዋት እንዲሸፈኑ ተደርጓል፡፡”

በወንዝ ዳርቻው እየተካሄደ ባለው እርሻ የአስተዳደር ክፍል ኃላፊው አቶ ነቢል እንደገለፁልን፤ በአካባቢው ያለው እርሻ አብዛኛው በእንጆሪ ፍራፍሬ የተሸፈነ ነው፡፡ እንጆሪ ከተተከለ በኋላ ከሶስት እስከ አራት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለምርት የሚደርስ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ ለምግብነት የደረሰውን ምርት የማስተዋወቅ ስራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡

እንጆሪን በጥሬው መመገብ፣ ተፈጭቶ በጁስ መልክ በማዘጋጀት አሊያም በማርማራታ መልክ አሽጎ ለምግብነት ማቅረብ እንደሚቻል ያነሱት አቶ ነቢል፣ የወንዝ ዳርቻው እንደ እንጆሪ ያሉ የፍራፍሬ ምርቶችና አትክልቶችን በስፋት በማምረት በከተሞች የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል። ድርጅቱ በቀጣይም ምርቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በስፋት ለማቅረብ ማቀዱን ነው የገለፁት፡፡

ይህ የልማት ፕሮጀክት ከአካባቢ ጥበቃና ከምግብ ዋስትና ባሻገር ለበርካታ ወገኖችም የስራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በፍራፍሬ ምርቶችና አትክልቶች ስራው ላይም ከ100 እስከ 150 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከልም አብዛኞቹ የአካባቢው ነዋሪዎችና ሴቶች መሆናቸውን አቶ ነቢል አስረድተዋል፡፡

በእንጆሪ ልማቱ የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ወጣቶች መካከል የእንጦጦ ቁስቋም አካባቢ ነዋሪዋ ለምለም ገበየሁ አንዷ ናት፡፡ ከዚህ ቀደም በቀን ሥራ፣ በግንባታ ዘርፍ በለሳኝነት ስትሠራ መቆየቷን የምታነሳው ወጣት ለምለም፤ ቀደም ሲል አካባቢው ለዓይን የማይስብና በቆሻሻ የተሞላ ነበር፡፡ አሁን ግን ንጹሕና ውብ ገፅታን ተላብሷል። ከዚህም ባሻገር ማዕከሉ ለእሷ የዕለት እንጀራ ፈጥሮላታል፡፡ በማዕከሉ ውስጥ እንጆሪ በመንከባከብ በምታገኘው ገንዘብ ሕይወቷን እየመራች ትገኛለች፡፡

ሌላኛዋ በእንጆሪ ልማቱ የስራ ዕድል የተፈጠረላት የአካባቢው ነዋሪ ወጣት አማረች ገባል ትባላለች፡፡ ወጣቷ ኑሮን ለማሸነፍ በስደት ወደ አረብ ሀገራት በመሄድ ሰባት ዓመት ያህል ሰርታለች። ነገር ግን በሕይወቷ ጠብ ያለ ነገር አልነበረም፡፡ ከስደት መልስም በጉሊት ንግድና በኋላ በፅዳት ስራ በመሰማራት ሕይወቷን ስትመራ የቆየችው ወጣት አማረች፤ የወንዝ ዳርቻው የአካባቢውን ገፅታ ከመቀየር ባሻገር ለወጣቶችና እናቶች የስራ ዕድል እንደፈጠረላቸው ትናገራለች፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የቀለብ ግዴታ በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ

የኋላሸት ወሰኔ (ዐ/ህግ)

## መግቢያ

የቤተሰብ ሕግ ማኅበረሰብን ከሚገነቡ መሠረታዊ ምሰሶዎች አንዱ ነው። በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 213/1992) ውስጥ የተካተተው የቀለብ (Maintenance) ግዴታ፣ እንዲሁም የተራቆተ የሕግ ደንብ ሳይሆን ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ሰብዓዊ እሴቶችን ያቀፈ መሣሪያ ነው። ሕጉ የቀለብ ግዴታን ከጋብቻ እና ከዝምድና ትስስር ጋር በጥብቅ ያገናኛቸዋል። ዋና ዓላማውም መንግሥታዊ ያልሆነ፣ በቤተሰብ ደረጃ የሚዋቀር የማኅበራዊ ዋስትና መረብ (Social Safety Net) መዘርጋት ነው።

የቀለብ ሕግ ዋና ዓላማ ግለሰቦችን በገንዘብ መቅጣት ወይም በአንዱ ሀብት ላይ ሌላውን ማበልፀግ አይደለም፤ ይልቁንም የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- **የችግረኛን ሕልውና ማረጋገጥ (Human Dignity)፡-** ቀለብ ምግብን፣ ልብስንና መጠለያን ያካትታል። እነዚህ ደግሞ የአንድ ሰው በሕይወት የመኖር መብት (Right to Life) መገለጫዎች ናቸው። ሕጉ እነዚህ መሠረታዊ ነገሮች እንዲሟሉ በማድረግ የዜጎችን ሰብዓዊ ክብር ይጠብቃል።
- **የቤተሰብ አንድነትን ማጠናከር (Family Solidarity)፡-** አባላት በችግር ጊዜ እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ በማድረግ የቤተሰብ ትስስር በገንዘብ እጥረት ምክንያት እንዳይፈራርስ ያደርጋል።
- **በመንግሥት ላይ የሚወድቀውን ጫና መቀነስ፡-** በማደግ ላይ ባሉ አገሮች እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት ለሁሉም ችግረኛ ወይም አቅመ ደካማ ዜጋ ወርሃዊ አበል (Welfare) መክፈል አይችልም። ስለዚህ ሕጉ ይህንን ኃላፊነት ወደ ቤተሰብ ተቋም በማዞር ማኅበራዊ ቀውስን ይከላከላል።

**በወንድማማቾችና በእህትማማቾች መካከልም ቢሆን፣ አንደኛው ወገን ፍጹም አቅም ሲያጣና ሌላኛው ደግሞ የተረፈ ሀብት ሲኖረው የመረዳዳት ግዴታ በሕግ ተጥሏል**



### 1. የቀለብ ትርጉምና ይዘት (አንቀጽ 198)

በሕጉ አንቀጽ 198 መሠረት፣ ቀለብ ማለት ለሰውየው ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማቅረብ ማለት ነው። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ። እንደ አስፈላጊነቱ ለጤና ጥበቃ የሚሆን ወጪ።
- ለቀለብ ጠያቂው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከሆነ ደግሞ ለትምህርት የሚያስፈልግ ወጪ።

### 2. የቀለብ ግዴታ የሕግ ምንጮች (Sources of Obligation)

የቀለብ ግዴታ በዘፈቀደ የሚጣል ሳይሆን፣ ሕጋዊ ዕውቅና ካላቸው ሁለት ዋና ዋና ትስስሮች ይመነጫል።

#### ሀ. የጋብቻ ትስስር (Marital Relationship)

ጋብቻ በሕግ ፊት ሁለት ሰዎችን በአንድነት የሚያስር ውል ብቻ ሳይሆን፣ መብትና ግዴታን የሚያስከትል ተቋም ነው።

**የትዳር ዘመን ግዴታ (አንቀጽ 49)፡-** ባልና ሚስት በትዳር ውስጥ እያሉ አብሮ የመኖር፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ግዴታ አለባቸው። እያንዳንዱ ተጋቢ እንደ አቅሙ ለቤተሰቡ የጋራ ወጪ (ምግብ፣ ኪራይ፣ ሕክምና) የማበርከት ግዴታ አለበት። አንደኛው ወገን ገቢ የሌለው ቢሆን እንኳን፣ በቤት ውስጥ በሚያበረክተው ጉልበትና አስተዋጽኦ ግዴታውን እንደተወጣ ይቆጠራል።

**ከፍቺ በኋላ የሚቀጥል ኃላፊነት (አንቀጽ 82 እና 206)፡-** ጋብቻ ሲፈርስ የመረዳዳት ግዴታው ወዲያውኑ አይቆምም። ፍቺው የተፈጸመው በአንደኛው ወገን ጥፋት ቢሆን እንኳን፣ ሌላኛው ወገን በከባድ ችግር ምክንያት ራሱን መርዳት ካልቻለ፣ ፍርድ ቤቱ ለተወሰነ ጊዜ (ከ6 ወር ለማይበልጥ) ቀለብ እንዲከፈል ሊያዝ ይችላል። ይህ ድንጋጌ ጋብቻ የፈጠረውን ሰብዓዊ ትስስር ሕጉ ከግምት ውስጥ እንደሚያስገባ ያሳያል።

#### ለ. የዝምድና ትስስር (Consanguinity and Affinity)

የኢትዮጵያ ሕግ ማኅበረሰባዊ ትስስርን መሠረት በማድረግ የቀለብ ግዴታን ወደ ዝምድና ሰንሰለቶች ያስፋፋል (አንቀጽ 197 )።

- **ወደ ታች የሚቆጠር ዝምድና (Descendants)፡-** ወላጆች ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወይም ራሳቸውን መቻል የማይችሉ ልጆቻቸውን የማሳደግና ቀለብ የመስጠት ተፈጥሯዊና ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው።
- **ወደ ላይ በሚቆጠር ዝምድና (Ascendants)፡-** ወላጆች ወይም አያቶች አቅመ ደካማ ሲሆኑና ራሳቸውን ማስተዳደር ሲሳናቸው፣ አዋቂ ልጆቻቸው ወይም የልጅ ልጆቻቸው ቀለብ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። ይህ በባሕላችን ያለውን "ወላጅን መጦር" የሚለውን እሴት ሕጋዊ ቅርጽ የሰጠ ነው።
- **የጎንዮሽ ዝምድና (Siblings)፡-** በወንድማማቾችና በእህትማማቾች መካከልም ቢሆን፣ አንደኛው ወገን ፍጹም አቅም ሲያጣና ሌላኛው ደግሞ የተረፈ ሀብት ሲኖረው የመረዳዳት ግዴታ በሕግ ተጥሏል።

### 3. የቀለብ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች (አንቀጽ 199 እና 200)

ቀለብ እንዲከፈል ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ሁለት ዋና ነጥቦችን ማረጋገጥ አለበት፡-

- **የጠያቂው ችግር (አንቀጽ 199)፡-** ቀለብ ፈላጊው በራሱ ጥረት ወይም ባለው ንብረት ራሱን ማስተዳደር የማይችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት።
- **የከፋዩ አቅም (አንቀጽ 200)፡-** ቀለብ እንዲከፍል የሚጠየቀው ሰው የራሱንና በኃላፊነቱ ሥር ያሉትን ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎት ካሟላ በኋላ የመክፈል አቅም ሊኖረው ይገባል።

### 4. የቀለብ መጠንን ስለመቀየር (አንቀጽ 204)

የቀለብ መጠን በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል። የቀለብ ከፋዩ አቅም ከቀነሰ ወይም የጠያቂው ፍላጎት ከበፊቱ ከጨመረ፣ አንደኛው ወገን የቀለብ መጠኑ እንዲቀንስ ወይም እንዲጨምር ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።

### 5. አከፋፈል ሁኔታ (አንቀጽ 205)

እንደ አጠቃላይ፣ ቀለብ በገንዘብ እና በየወሩ የሚከፈል ነው። ሆኖም ግን፣ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ቀለቡ በዓይነት (ለምሳሌ በመኖሪያ ቤት ወይም በምግብ) እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል።

### 6. የቀለብ ግዴታ ማቆሚያ ምክንያቶች (አንቀጽ 211 - 213)

የቀለብ ግዴታ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

- ቀለብ ተቀባዩ ራሱን መቻል ሲጀምር።
- ቀለብ ከፋዩ የመክፈል አቅሙን ሲያጣ።
- ከባለዕዳዎቹ አንደኛው ሲሞት (አንቀጽ 213)።
- ቀለብ የምትቀበለው የተፋታች ሚስት ከሆነችና ዳግም ጋብቻ ስትመሰርት።

### ለተግባራዊ ሥራ የሚረዱ ተጨማሪ ነጥቦች

**አንቀጽ 208 (የቀለብ ቅደም ተከተል)፡-** ብዙ ሰዎች ቀለብ የመስጠት ግዴታ ካለባቸው (ለምሳሌ ብዙ ልጆች)፣ ግዴታው በመካከላቸው እንደ አቅማቸው ይከፋፈላል።

**አንቀጽ 210 (የመጠየቂያ ጊዜ)፡-** የቀለብ መብት ካለፈው ጊዜ ይልቅ ለወደፊቱ ጊዜ ነው የሚታሰበው። ሆኖም ግን ክስ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ሊያካትት ይችላል።

# ወቅታዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

በሳህሉ ብርሃኑ

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በአገሪቱ ወቅታዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ የሰጠበትን መግለጫ በትናንትናው ዕለት አወጥቷል። ጽሕፈት ቤቱ በዚሁ መግለጫው በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ እየታዩ ያሉ ዋና ዋና ሁነቶችን በመዳሰስ፣ የተመዘገቡ ስኬቶችንና እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችን ለመፍታት እየተወሰዱ ስላሉ እርምጃዎች በዝርዝር አስታውቋል። የመግለጫው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም ማለዳ ላይ፤ የመጀመሪያው የወገግታ ጭላንጭል በከፍታማዎቹ የኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ፈንጥቆ ጨለማውን ሳይቀድ በፊት ኢትዮጵያውያን ረጃጅም ሰልፍ ተሰልፈዋል። በጅማ፣ በድሬዳዋ፣ በሐዋሳ፣ በባሕር ዳር እንዲሁም ስማቸው በዓለም አቀፍ የዜና ጋዜጣዎች ላይ ፈጽሞ ሊወጣ በማይችሉ ከተሞችና መንደሮች ውስጥ ያሉ ወንዶችና ሴቶች፤ ወሳኝ ተግባር ለመፈጸም በሰልፍ ቆሙ። ድምፅ ሰጡ! ይህንን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከአምሳ አራት ሚልዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች ተመዝግበው ነበር። ይህ ቁጥር ከአንዳንድ አገሮች አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር በላይ ነው። ይህ ምርጫ እውነተኛ ስለመሆኑ ጥያቄ ለሚያነሣ ለማንኛውም አካል ግልጽ እና የማያሻማ ምላሽ ሰጥቷል!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ52 ሺህ ምርጫ ጣቢያዎች መካከል ከ50 ሺህ 188 በላይ የሚሆኑት በሰዓቱ ተከፍተው ቀኑን ሙሉ መራጮችን ሲያስተናግዱ እንደነበር አረጋግጧል። ከ42 የፖለቲካ ፓርቲዎች የተወጣጡ ከ10 ሺህ 438 በላይ ዕጩዎች እና 80 የግል እጩዎች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት ወንበሮችን ለማሸነፍ ተወዳድረዋል። ይህ በማንኛውም ሊለካ በሚችል መሥፈርት በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቁ እና በውሳኔ አሰጣጥም ሆነ በአስተዳደራዊ ረገድ እጅግ በረቀቀ ሁኔታ ተግባራዊ የተደረገ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ የታየበት ኩነት ነበር።

የቀድሞው የኬንያ ፕሬዝዳንት ክቡር ኡሁሩ ኬንያታ የሚመሩትና ከ37 የአፍሪካ ሀገሮች የተወጣጡ 83 ታዛቢዎችን ያቀፈው የአፍሪካ ኅብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምርጫውን "ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን በሰፊው በሚደግፍ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ውስጥ የተካሄደ" ሲል ገምግሞታል። በቀድሞዋ የኡጋንዳ ምክትል ፕሬዝዳንት ክብርት ዶክተር ስፔሲዮዛ ዋንዲራ ካዚብዌ የሚመራው የኢጋድ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ባወጣው የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በታዘቡባቸው ጣቢያዎች ሁሉ የምርጫ ሳጥኖች በትክክል የታሸጉ መሆናቸውን፣ የፓርቲ ወኪሎች በሂደቱ በሙሉ መገኘታቸውን እንዲሁም ምርጫው አስደናቂ ተቋማዊ፣ አስተዳደራዊና የቴክኖሎጂ ዕድገትን ያሳየ መሆኑን አረጋግጧል። የኢጋድ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ይሄንን ምርጫ "የበርካታ አዳዲስ ምዕራፎች ምርጫ" ሲል ሰይሞታል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በድምፅ መስጠት ሂደት ውስጥ ምንም ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳልተመለከተ አረጋግጧል።

የሲቪክ ማኅበረሰብ ታዛቢዎች ጥምረት በምርጫ ቦርድ እውቅና ከተሰጣቸው 55 ድርጅቶች 65 ሺህ 299 ታዛቢዎችን በመላ ሀገሪቱ ያሠማራ ሲሆን፣ 99 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያለምንም ዕንቅፋት የመታዘብ ዕድል ማግኘቱን አረጋግጧል። እነዚህ ተዓማኒነት ያላቸው ሀገራዊ እና አኅጉራዊ ተቋማት ያደረጓቸው ግምገማዎችና የሰጧቸው እውነተኛ ፍርዶች ናቸው። እነዚህ ለአፍሪካ ጥላቻ ካላቸው ወይም የአፍሪካን ዴሞክራሲ በውጫዊ መሥፈርቶች ከሚለኩ ተቋማት የተደመጡ ድምፆች አይደሉም።

አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተንታኞች ይህንን ምርጫ እንደ ንግሥና በዓል አድርገው ያቆሸሹት ሲሆን፣ ውጤቱም አስቀድሞ የተወሰነ ድራማ እንደነበር አድርገው ሊያቀርቡት ሞክረዋል። እነዚህ መግለጫዎች ከእውነታው ፈጽሞ የራቁ፣ በጥናትና ትንተና ላይ ያልተመሰረቱ እንዲሁም ነፃና የታሰበበት ዴሞክራሲያዊ ምርጫቸውን በኩራት ላደረጉ በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ክብር የማይሰጡ በመሆናቸው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሙሉ በሙሉ የማይቀበላቸው መሆኑን ያረጋግጣል። አስቀድሞ የተወሰነ ውጤት ቢኖር ኖሮ፤ ከ37 የአፍሪካ ሀገሮች የተወጣጡ 83 ገለልተኛ ታዛቢዎችን፣ 65 ሺህ 299 የሀገር ውስጥ የሲቪል ማኅበረሰብ ታዛቢዎችን ወይም 1 ሺህ 100 ዕውቅና የተሰጣቸውን ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች መጋበዝ ባላስፈለገ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዚህ ሀገራዊ ምርጫ ለተሳተፉ የኢትዮጵያ ዜጎች፣ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ላሠማራቸው ከ350 ሺህ በላይ ኃላፊዎች፣ ሂደቱን ለጠበቁት የጸጥታ ኃይሎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ግንባታ መኀልበት እና ለሂደቱ መሳካት ያላትን ቁርጠኝነት ላረጋገጡት የአፍሪካ እና ቀጣናዊ የታዛቢ ቡድኖች ምስጋናቸውን ያቀርባሉ!

## ስለ ኢትዮጵያ ልማት

ኢትዮጵያውያን ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም ውሳኔያቸውን ሲያስቀምጡ፣ ሀገራቸውን በፍጹም የዴሞክራሲ ባህል ውስጥ ለማንበር ነው። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ባላት ጸጋ ልክ የሚያስፈልጋትን ሁለንተናዊ ልማት በፍጥነት እውን የማድረግ ባህል እንዲቀጥል ሕዝባችን ተናግሯል።

ባለፉት ዓመታት የታየው እውነት እንደሚያሳየን የኢፌዴሪ መንግሥት የተስፋ ቃል መንግሥት አልነበረም። ይልቁንም በተጨባጭ የሚታዩ ውጤቶች የተመዘገቡበት ውጤት ተኮር መንግሥት ሲሆን፤ እነዚህም ውጤቶች በግልጽ የሚታዩ ናቸው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2017 በጀት ዓመት የ9 ነጥብ 2 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ ይህም በዓለም ላይ ፈጣን ዕድገት ካስመዘገቡ ኢኮኖሚዎች አንዱ ያደርገዋል። ይህንን መነቃቃት መሠረት በማድረግ በ2018 በጀት ዓመት የኢኮኖሚ ዕድገቱ 10 ነጥብ 2 በመቶ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል። ዕድገቱ ግብርናን፣ ኢንዱስትሪንና የአገልግሎት ዘርፎችን በከፍተኛ ደረጃ ያካተተ ሰፊ መሠረት ያለው ቢሆንም፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን ኢንዱስትሪው ለዕድገቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይል ሆኖ እየመጣ ይገኛል። ይህም መንግሥት ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለኢንዱስትሪ ልማት፣ ለዕሴት ጭማሪና ለውጭ ገበያ ተኮር ምርቶች የሰጠውን ቀጣይነት ያለው ትኩረት ያሳያል።

እነዚህ ውጤቶች እንዲሁ ግምቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የ100 ቀናት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት አማካኝነት ክትትል የሚደረግባቸው የተጠያቂነትና የታቀደ አመራር ፍሬዎች ናቸው። አጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ 20 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ከ2016 ዓ.ም ወዲህ የ100 በመቶ ገደማ ጭማሪ አሳይቷል። የዋጋ ግሽበትም ወደ ታች ማሽቆልቆሉን በመቀጠል አሁን ላይ ወደ አንድ አሐዝ ደረጃ እየተቃረበ ይገኛል፤ ይህም በቅርብ ዓመታት ውስጥ በቤተሰቦችና በንግዶች ላይ ከባድ ጫና ፈጥሮ ከነበረው ባለ ሁለት አሐዝ የዋጋ ግሽበት አንጻር ትልቅ መሻሻል ነው። ይህ ስኬት የተመዘገበው ዓለም አቀፍ የኃይል አቅርቦትና ሌሎች ስትራቴጂካዊ ቁሳቁሶችን ገበያ ያናጋው የመካከለኛው ምስራቅ ወቅታዊ ጂኦ ፖለቲካዊ ውጥረትን ጨምሮ፣ ውጫዊ ጫናዎች በነበሩበት ወቅት ነው።

የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ከተጀመረ ወዲህ መንግሥት ከውጭ ምንጮች ምንም ዓይነት አዲስ የንግድ ብድር ስምምነት ያላደረገ ሲሆን፣ ይህም የሀገሪቱን የብድር ዕዳ ጫና በከፍተኛ ሁኔታ አቅልሎታል። ከእነዚህ ቁጥሮች በስተጀርባ ኢትዮጵያውያን በዓይናቸው የሚያዩትና በእጃቸው የሚዳስሱት ተጨባጭ ለውጥ አለ። ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለመኖሪያ ቤቶች፣ ለንግድ ተቋማትና ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጨ ይገኛል። ይህ ግድብ በራሳቸው በኢትዮጵያውያን የተደገፈ፣ በኢትዮጵያውያን መሐንዲሶች የተገነባና ቀጣይነት የነበረውን ውጫዊ ጫናዎችን ተቋቁሞ የተጠናቀቀ ነው። ከሃይድሮ ፓወር ጎን ለጎን፣ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል የሚገኘውን የአይሻ ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ እና በአርሲ ዞን የሚገኘውን የአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፤ በመሳሰሉ ሥራዎች የታዳሽ ኃይል አቅርቦቷን እያሰፋች ሲሆን፣ ይህም የቀጣናዊ ኢነርጂ ትብብርን እያሳደገ የብሔራዊ ኃይል አቅርቦት መረቡን የመቋቋም ዐቅም ያጠናክራል። በአፍሪካ አህጉር ታሪክ ውስጥ ትልቁ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት አንዱ የሆነው የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ግንባታው ተጀምሯል። እነዚህ ምኞቶች አይደሉም፤ ተጨባጭ ሐቆች ናቸው።

## ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪና ቴክኖሎጂ

በግብርናው ዘርፍ፣ የመንግሥት የምግብ ሉዓላዊነት አጀንዳ ወቅታዊ ለውጦችን ሳይሆን መዋቅራዊ ውጤቶችን እያስገኘ ቀጥሏል። በሶማሌ ክልል የጎዴ ዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካን ለመገንባት ከአሊኮ ዳንጎቴ ግሩፕ ጋር የተፈረመው አጋርነት የዘመኑ ጉልህ የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች አንዱ ማረጋገጫ ነው። ፋብሪካው በዓመት 3 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ዩሪያ የማምረት አቅም እንዲኖረው ታቅዶ እየተገነባ ሲሆን፣ ይህም ኢትዮጵያን በዓለም ትላልቅ ማዳበሪያ አምራች ሀገራት ተርታ ያሰልፋታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግንቦት 9 ቀን 2018 ዓ.ም የፕሮጀክቱን የግንባታ ሂደት በጎበኙበት ወቅት እንደገለጹት፤ "ይህ ፕሮጀክት በግብርና ትራንስፎርሜሽን፣ በምግብ ዋስትና፣ በኢንዱስትሪ ዕድገትና በኢኮኖሚ ራስን መቻል ላይ የተደረገ ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ነው" ብለዋል። አስተማማኝ ባልሆነና ውድ በሆነ የማዳበሪያ አቅርቦት ለረጅም ጊዜ ለተገደቡት ኢትዮጵያውያን አምራቾች የዚህ ፕሮጀክት ፋይዳ ፈጣንና ተጨባጭ ነው።

ከዚህ ምርጫ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግንቦት 19 ቀን 2018 ዓ.ም በነገሌ ቦረና ገዳ አውሮፕላን ማረፊያ ምርቃት ላይ ሲገኙ የታየው ተምሳሌትነት ለቦረና ሕዝብ ትልቅ ትርጉም ነበረው። ይህ ዞን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅበት ስም የሀገርን አንገት ያስደፋ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ሲሆን፤ እርሱም ድርቅ ነው። ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የዝናብ መጥፋት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ከብቶችን የገደለ፣ ቤተሰቦች ለውኃ ፍለጋ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን እንዲጓዙ ያስገደደ፣ እንዲሁም በእነዚህ የግጦሽ መሬቶች ላይ ለዘመናት ራሳቸውን ችለው የኖሩ ማኅበረሰቦችን ለአስቸኳይ የምግብ እርዳታ እጅ እንዲዘረጉ አድርጎ ነበር። ዓለም የሚያውቃት ቦረና እርሷ ነበረች። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግንቦት ወር ጉብኝት ግን የተለየ ታሪክ አሳይቷል። አሁን ላይ ለአርብቶ አደር ማኅበረሰቦችና ለከብቶቻቸው ንጹሕ ውኃ እያቀረቡ ያሉትን የውኃና የመስኖ መሠረተ ልማቶችን የገመገሙ ሲሆን፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት አቧራ ብቻ በነበረው መሬት ላይ የክላስተር እርሻዎችን ጎብኝተዋል፤ በያቤሎ የባህል ማዕከል መርቀዋል፤ እንዲሁም በአየር ንብረት ሁኔታዎች ምክንያት ቀድሞ ተገልሎ ለነበረው ቀጣና ዓመቱን ሙሉ ትስስር የሚፈጥር አውሮፕላን ማረፊያ መርቀው ከፍተዋል።

የአምራች ዘርፉም ተመሳሳይ የለውጥ ታሪክ አለው። በግንቦት 2018 ዓ.ም በተካሄደው 4ኛው ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ላይ፤ መንግሥት ለአራት ዓመታት የተመዘገበውን ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ መስፋፋት ውጤቶች አቅርቧል። የአምራች ዘርፉ የግብዓት አቅርቦት በዓመት ከ9 ሚሊዮን ቶን ወደ 15 ሚሊዮን ቶን አድጓል። የምርት አቅም አጠቃቀም ከ47 በመቶ ወደ 67 በመቶ ከፍ ማለቱን፣ የማኑፋክቸሪንግ ዕድገት ከ4 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 10 ነጥብ 7 በመቶ ማደጉን፣ እንዲሁም ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርበው ፋይናንስ ከ8 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ወደ 50 ቢሊዮን ብር ማደጉን ያሳያል። እነዚህ ስኬቶች በሀገር ውስጥ ምርት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንጸባረቁ ይገኛሉ። ኤክስፖው በተጠናቀቀ በሃያ ቀናት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ብቻ ተጠናቆ ከ80 በመቶ በላይ ጥሬ ዕቃውን ከሀገር ውስጥ የሚያገኘውን ግዙፍ የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት "ግራንዲዩር የሴራሚክ ማኑፋክቸሪንግ" ፋብሪካን በሞጆ ከተማ መርቀዋል። ቀደም ሲል በገቢ የሴራሚክ ምርቶች ላይ ጥገኛ የነበረችው ኢትዮጵያ አሁን ላይ የሴራሚክ ምርቶችን ከውጭ ማስገባት ሙሉ በሙሉ ለማቆምና ለውጭ ገበያ የሚሆን ምርት ለማስፋፋት እየተዘጋጀች ትገኛለች። በቴክኖሎጂው ዘርፍም ዘመናዊ ልማት ከጊዜ ወደ ጊዜ በዳታ፣ በፈጠራና በዲጂታል ሥርዓቶች የሚወሰን መሆኑን በመገንዘብ መንግሥት ኢትዮጵያን ሰው ሠራሽ አስተውሎት እና የኢንዱስትሪ 5 ማሕቀፎችን ቀድመው ከተገበሩ ሀገራት ተርታ እያሰለፋት ይገኛል።

## የጽንፈኝነትን ፖለቲካ ውድቅ ማድረግ

በኦነግ ሸኔ ዐማጽያን በንጹሐን ዜጎች ላይ በተለይም በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ዒላማ ተደርገው የተፈጸሙ ጥቃቶችን ተከትሎ፤ የቤተሰብ እና የወዳጆቻቸውን ሕይወት ላጡ፣ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው እና የቤት ንብረታቸው ለወደመባቸው በአርሲ ዞን ለሚገኙ ወገኖቻችን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ መንግሥት ስም የተሰማቸውን ጥልቅ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

# ስኩተር አዲሱ የትራንስፖርት አማራጭ

- **በመዲናዋ በኮሪደር ልማቱ ከ241 ኪሎ ሜትር በላይ የሳይክልና የስኩተር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መንገድ ተሰርቷል፤**

**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባ በፈጣን የእድገትና ለውጥ ሀዲድ ውስጥ ትገኛለች። ለውጡ በመንገዶች፣ በህንጻዎችና መሰል መሠረተ ልማቶች መዘመን፣ ንጹህና ውብ ገፅታ መላበስ ብቻ የታጠረ ሳይሆን በነዋሪዎቿ የኑሮ ዘይቤና ልምድም ይታያል። ለዚህም በትራንስፖርት አጠቃቀም ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማሳያነት ማንሳት ይቻላል።



ፎቶ- ከፋይል

በመዲናዋ ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎችን እንደ አንድ የትራንስፖርት አማራጭ መጠቀም እየተለመደ መጥቷል

አቶ ተስፋ በላይነህ ነዋሪነታቸው በአዲስ አበባ መገናኛ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። የንግድ ሰውም ናቸው። በኮሪደር ልማት የተሰሩ መሠረተ ልማቶች ለእግረኞች፣ ሳይክልና ስኩተር ተጠቃሚዎች እንቅስቃሴ ምቹ እድል ፈጥሯል። እንደ ንግድ ሰውም በሳይክልና ስኩተር ዘርፍ ለመሰማራት ሀሳብ እንዳላቸው ያነሳሉ።

አቶ ተስፋ በአንድ ወቅት የግል መኪናቸው ተበላሽቶ ለማሰራት ጋራዥ በገባችበት ወቅት ቁርቆስ ክፍለ ከተማ የሚያስፈፅሙት አንድ አስቸኳይ ጉዳይ ነበራቸው። በቶሎ መድረስ ስለነበረባቸው እንደ አማራጭ አድርገው የወሰዱት ወደፊት ሊሰሩበት የሚመኙትን የስኩተር ትራንስፖርትን መጠቀም ነው። ከመገናኛ ስኩተር በመከራየት መስቀል አደባባይ በ15 ደቂቃ ደርሰው፣ በ10 ደቂቃ ተስተናግደው፣ እንደገና በ15 ደቂቃ ወደ ቤታቸው መመለሳቸውን በማስታወስ ጉዳያቸውን ለመጨረስ አጠቃላይ 40 ደቂቃ ወስዶባቸዋል። ለአንድ የደርሶ መልስ ጉዞ 105 ብር ከፍለዋል። ይህም በታክሲ ወረፋና ትራንስፖርት መጨናነቅ ሊባክን የነበረውን ጊዜ እንዲቆጥቡ አድርጓቸዋል።

"ስኩተር ሊበረታታ የሚገባ፣ ምቹ እየሆነች ለመጣችው ከተማ የሚመጥን ትራንስፖርት ነው። እኛም እንደ ነዋሪ ሞተር አልባ የትራንስፖርት አማራጮችን ለመጠቀም ዝግጁ መሆን አለብን" ያሉት አቶ ተስፋ፣ ለቴክኖሎጂ ቅርብ መሆናቸውንና በቀላሉ ተለማምደው መጠቀም መጀመራቸውንና ጓደኞቻቸውም ፈለጋቸውን ተከትለው መጠቀም እንደጀመሩ አንስተዋል።

በተለያዩ ጊዜያት ቦርሳቸውን በጀርባ አዝለው ጉዳያቸውን ለማስፈፀም ስኩተርን በመጠቀም ወደ መስቀል አደባባይ መሄዳቸውን የሚገልጹት አቶ ተስፋ፣ "የኮሪደር ልማቱ ለሞተር አልባ ትራንስፖርት መልካም እድል ስለፈጠረ እንደ መዝናኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገራት ከተሞች እንደሚታየው እንደ አንድ የትራንስፖርት አማራጭ ማስፋፋት ቢቻል አዋጪና አትራፊ ነው። የአጠቃቀም የደህንነት ህግ እንዲወጣለት ያስፈልጋል" ሲሉ በቀጣይ ቢሰሩ ያሉትን ጭምር አብራርተዋል።

ወጣት ነብዩ ሳሙኤል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ጨፌ ኮንዶሚኒየም እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው። ለደንበኞች የተለያዩ ዕቃዎችን ባሉበት ቦታ በማድረስ በሚሰራ የዴሊቨሪ ድርጅት ተቀጥሮ ይሰራል። ለዚህም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ስኩተርን እንደ ትራንስፖርት አማራጭ ይጠቀማል። ብዙውን ጊዜ ከመገናኛ ወደ አትላስ፣ ከመገናኛ ወደ መስቀል አደባባይ ዕቃዎችን ያደርሳል። በጉዳዩ ላይ በሰጠው አስተያየትም፣ "ስኩተር የመንገድ መጨናነቅ ሳያሳስበን በፍጥነት የፈለግነው ቦታ መድረስ የሚያስችል፣ ለአጠቃቀም ቀላል፣ ከብክለት ነጻ የሆነ የተሽከርካሪ ዓይነት ነው" ብሏል።

በኮሪደር ልማት የተሰሩ የሳይክል መንገዶች ስኩተር ለመጠቀም ምቹ እንደሆኑ የሚናገረው ወጣት ነብዩ፣ ከስራ ባሻገር አንዳንድ ጊዜ ምሽት ላይ በስኩተር እየተንቀሳቀሰ ይዝናናል። ለአገልግሎቱ የሚጠየቀው ክፍያም ቢሆን ከታክሲ አኳያ በቶሎ የፈለገበት ቦታ ለመድረስ ስለሚያስችለው ተመጣጣኝ የሚባል ነው። እንደዚህ ዓይነት የትራንስፖርት አማራጮች መበራከት አለባቸው። ከዚህ ባሻገር በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ስኩተሮችን መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር መስራት እንደሚያስፈልግ ገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባወጣው የብስክሌት መጋራትና የብስክሌት መስመር አጠቃቀም ደንብ 183/2015 ላይ እንደተቀመጠው፣ ስኩተር ማለት በኤሌክትሪክ ባትሪ የሚንቀሳቀስ ባለ ሁለት ጎማ ሆኖ ተሳፋሪው ቆሞ የሚነዳው ተሽከርካሪ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ዳግም በልሁ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ስኩተር አንድ ሰው በቀላሉ ሊያሽከረክረው የሚችል፣ ልክ እንደ ብስክሌት አገልግሎት የሚሰጥ፣ በሰዓት እስከ 25 ኪሎ ሜትር መንቀሳቀስ የሚችል፣ የአደጋ ተጋላጭነት የሌለው፣ የትራፊክ መጨናነቅ የማያግደው ሞተር አልባ የተሽከርካሪ ዓይነት ነው። በኤሌክትሪክ አማካኝነት የሚሰራ ሲሆን አንድ ጊዜ ቻርጅ ከተደረገ እንደየ ስኩተሩ ባህሪ ከ60 እስከ 80 ኪሎ ሜትር በመጓዝ የሚችል ነው።

## ዘርፉን ለማስፋፋት ምን እየተሰራ ነው?

የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አቶ ዳግም እንደሚናገሩት፣ በአዲስ አበባ ከዚህ ቀደም የነበረው ትራንስፖርት ባለአራት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ የተንጠለጠለ ነበር። መንገዶችም ዲዛይን ሲደረጉና ሲገነቡ ተሽከርካሪዎች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ለእግረኞች ምቹ አልነበሩም። የኮሪደር ልማቱ ከአራት እግር ተሽከርካሪዎች ባሻገር እንደ ሳይክልና ስኩተር ያሉ ያለ ነዳጅ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች፣ በእግር ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በጥቅሉ ለሞተር አልባ ትራንስፖርት ትልቅ አቅም ፈጥሯል።

በመዲናዋ በኮሪደር ልማቱ ከ241 ኪሎ ሜትር በላይ የሳይክልና የስኩተር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መንገድ ተሰርቷል። በከተማዋ ጠዋትና ከሰዓት ከ9፡00 ሰዓት በኋላ ሰፊ የሆነ የትራፊክ እንቅስቃሴ ይታያል። ከዚህ አኳያ ነዋሪዎች ሳይጨናነቁ በእግራቸውና በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች የሚንቀሳቀሱበት ዕድል ተፈጥሯል። በተለይ የሞተር አልባ ትራንስፖርት እንቅስቃሴን በሕግና በሥርዓት ለመምራትም የብስክሌት መጋራትና የብስክሌት መስመር አጠቃቀም ደንብ 183/2015 እንዲዘጋጅ መደረጉን አቶ ዳግም ያስረዳሉ።

ደንቡ በከተማዋ የተሽከርካሪ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ምክንያት የሚያጋጥመውን የትራፊክ እንቅስቃሴ መጨናነቅ ለማቃለል፣ የአካባቢ አየር ብክለትን ለመቀነስ፣ ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን ለማቀላጠፍ፣ የአካል ብቃትን ለማዳበር፣ የአዕምሮ እድገትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ጥቅሞችን የሚያስገኙ የሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎትን ማስፋፋት ዓላማ አለው። በተጨማሪም የሞተር አልባ ትራንስፖርት የትራንስፖርቱ አንድ አካል ሆኖ አገልግሎት እንዲሰጥ፣ የግሉን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች ለማበረታታት፣ ተጠቃሚው ኅብረተሰብም ከመዝናናት ባለፈ በዕለት ተዕለት ሕይወቱ በሚያደርገው እንቅስቃሴ መጠቀም እንዲችል ዓላማ ያለው ነው።

በደንቡ መሠረትም በሞተር አልባ ትራንስፖርት የሚሰማሩ ባለሀብቶች (ኦፕሬተሮች) ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ወደ ስራ ገብተዋል። በስኩተር ደረጃ በአሁኑ ወቅት ሁለት ድርጅቶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በብስክሌት ትራንስፖርት ረገድ ቀድመው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ አሉ፤ በቅርቡም በአንድ ባለሀብት ከ100 በላይ አረንጓዴ ብስክሌቶች ተሰማርተዋል። እነዚህ ብስክሌቶች ከመስቀል አደባባይ- ደምበል- ወሎ ሰፈር እስከ ቦሌ ስካይ ላይት ሆቴል ድረስ ባሉ አካባቢዎች ሽፋን የሚሰጡ ናቸው። ስኩተሮችም ከመስቀል አደባባይ አንስቶ ደምበል- ወሎ ሰፈር- ቦሌ እስከ መገናኛ ድረስ እንዲሁም በውስጥ አትላስ አካባቢ በመሸፈን አገልግሎት ይሰጣሉ።

ሰዎች እነዚህን የትራንስፖርት አይነቶች ቀለል አድርገው የሚያዩአቸው ቢሆንም አዘውትረው እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ስኩተሮችንና ብስክሌቶችን ከዚህ ቀደም እንደ መዝናኛ እንጂ የትራንስፖርት አካል ተደርገው አይታዩም ነበር። በብዛትም የውጭ ዜጎችና ወጣቶች ለመዝናናት ነበር የሚጠቀሙባቸው። በአሁኑ ወቅት ግን በመደበኛነት የትራንስፖርት አካል ሆነው እየተገለገሉባቸው ይገኛሉ። የፋይዳ መታወቂያ ያለው ማንኛውም ሰው መጠቀም የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል።

ከመስቀል አደባባይ ወደ ቦሌ ያለ ምንም የመንገድ መጨናነቅ ስጋት በስኩተርና ሳይክል መሄድ ይቻላል። ተሽከርካሪዎችን 'ወስጄ የት አስቀምጣለሁ ወይም እመልሳለሁ' የሚል ስጋት የለም። ምክንያቱም ተሽከርካሪዎቹ የእንቅስቃሴ መከታተያ መሳሪያ (ጂፒኤስ) የተገጠመላቸውና በዲጂታል መንገድ ክትትል የሚደረግባቸው ናቸው። አገልግሎቱን ለመጠቀምም ሆነ ክፍያ ለመፈፀም ተጠቃሚው የአገልግሎት ሰጪውን መተግበሪያ በስልኩ ላይ በመጫን መክፈል ይችላል፡፡

እንደ ስኩተርና ሳይክል ያሉ የትራንስፖርት አማራጮች ተደራሽነት በአሁኑ ወቅት በጅምር ደረጃ ነው የሚገኙት። በዘርፉ በርካታ አገልግሎት ሰጪዎች እንዲሰማሩ ይፈለጋል። በራሳቸው ገዝተው ለትራንስፖርት የሚጠቀሙ አሉ። በተጨማሪም በዘርፉ ለመሰማራት ጥያቄ ያቀረቡም አሉ። መንግሥትም በጅምር ላይ የሚገኘውን የሞተር አልባ ትራንስፖርትን እንደ አማራጭ ለማሳደግ እየሰራ እንደሚገኝ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

"ስኩተር ሊበረታታ የሚገባ፣ ምቹ እየሆነች ለመጣችው ከተማ የሚመጥን ትራንስፖርት ነው። እኛም እንደ ነዋሪ ሞተር አልባ የትራንስፖርት አማራጮችን ለመጠቀም ዝግጁ መሆን አለብን"

# ኪነ ጥበባዊ ማዕድ

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል ፣ የመጽሐፍት አውደ ርዕይ፣ የሥነ-ጥበብ አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡















ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጽሐፍት አውደ ርዕይ በመጪው ሰኞ ይጀመራል። አውደ ርዕዩ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ ሲሆን ከ40 በላይ መጽሐፍት ሻጮችና አከፋፋዮች እንደሚሳተፉበት ተገልጿል። የመጽሐፍት አውደ ርዕይ ሲካሄድ ለ18ኛ ጊዜ ሲሆን፤ መርሃ ግብሩ የሚካሄደው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ነው፡፡

በሌላ መረጃ የበእውቀቱ ስዩም ስብስብ ግጥሞች ላይ ውይይት ሊደረግ ነው፡፡ ውይይቱ የሚካሄደው በኦንላይን ሲሆን አዘጋጁ የኢትዮጵያ የመጽሐፍት ፎረም ነው፡፡ ውይይቱ በነገው ዕለት ምሽት ከ2፡00 ሰዓት እስከ 4፡00 ሰዓት ይደረጋል፡፡

## የስዕል አውደ ርዕይ

“ስውር መልክ” የስዕል አውደ ርዕይ በመጪው ሰኔ 7 ቀን 2018 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡ “ስውር መልክ” ወይም “ዘ ሂድን ፎርም” በተሰኘ መሪ ቃል የተዘጋጀው የሰዓሊ መሐሪ ተሾመ አውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው በቦሌ ብራስ ኬኬር ሆቴል ሕንጻ ሁለተኛ ፎቅ ላይ የሚገኘው አርታዊ ጋለሪ ነው፡፡

## የኪነ ጥበብ ውይይት

የኢትዮጵያ ሴት ሰዓሊያንና ቀራጺያን ማህበር ከአለ የሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ጋር በጋራ ያዘጋጁት የኪነ ጥበብና የፓናል ውይይት ዛሬ ይደረጋል። ውይይት የሚደረገው በአርቲስት መላኩ በላይ (ፊንድቃ) የሕይወትና የጥበብ ጉዞ ላይ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ የሚደረገው ዛሬ ከ4፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት ሲሆን፤ ቦታው ደግሞ አለ የሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ነው፡፡

## ሙዚቃ

“ጦሳ ላይ” የተሰኘው አዲስ ሙዚቃ ዛሬ ምሽት ይለቀቃል፡፡ የድምፃዊ ተስፋልደት ታደሰ ስራ የሆነው “ጦሳ ላይ” ዛሬ ማታ በናሆም ሬከርድስ አማካኝነት ለአድማጭ ተመልካች ይደርሳል፡፡ የዜማ ደራሲው ሰለሞን አድማሱ ሲሆን ግጥሙን የጻፈው ደግሞ እልፍግድ እምሻው ነው፡፡ ድምፃዊ ተስፋልደት ታደሰ የፋና ላምሮት ድምፃዊያን ውድድር አሸናፊ መሆኑ ይታወቃል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሑድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። ቅዳሜ “12ቱ እንግዶች” ቴአትር በ8፡00 ሰዓት እና በ12፡00 ሰዓት ይታያል። እሑድ በ7፡30 ሰዓት “ንጉሥ አርማህ” ቴአትር፣ እንዲሁም “እምዬ ብረቷ” የተሰኘው ቴአትር በ11፡30 ሰዓት ላይ ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ለሚታዩ ቴአትሮች ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ በ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያ በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል። በተጨማሪም ባልቻ አባነፍሶ ቴአትር እሑድ በ8:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የሚታይ ሲሆን፤ የክፍያ ስርዓቱን በኦን ላይን ማካሄድ እንደሚቻል ተገልጿል፡፡

በሀገር ፍቅር ቴአትር ደግሞ “ነገሩ አይቆምም” ሐሙስ 11፡30 ሰዓት፣ “ሰዴታ(በአፋን ኦሮሞ) እሑድ 8፡00 ሰዓት እንዲሁም የመጨረሻው ፍርድ እሑድ 12፡00 ሰዓት ለቴአትር አፍቃሪያን ይታያል፡፡ በተጨማሪም “አዮ ቦራ” የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ የህጻናት ቴአትር ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት በህጻናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ለእይታ ይቀርባል። በተመሳሳይ “የሰማይ ልጆች” የተሰኘው ቴአትር እሑድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ፍላሚንጎ በሚገኘው በህጻናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ይታያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው (3×1)+(5×2)+(2×3)+(6×4)=43 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ (4×1)+(2×2)+(1×3)+(7×4)=39 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ የመጨረሻው (8×1)+(6×2)+(5×3)+(3×4)=47 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **47** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ከተፈጥሮ ጋር የተወዳጁ መስህቦች

**በጊዜው አማረ**

በአሁኑ ወቅት የዓለም የመዝናኛ ባህል ከአዳራሽ ውስጥ ወጥቶ ወደ ተፈጥሮ እየሄደ ነው፡፡ የሰው ልጅ በቴክኖሎጂና በከተማ ኑሮ ግርግር ውስጥ የሚደርስበትን የአእምሮና የሰውነት ድካም ለመቅረፍ፣ በአረንጓዴ ተክሎችና በንጹሕ አየር የተከበቡ ስፍራዎችን ተመራጭ የመዝናኛ ስፍራ እያደረገ መጥቷል። ይህ ዓይነቱ የተፈጥሮ መዝናኛ የሰውን ልጅ መንፈስ ከማደስ ባለፈ፣ አካባቢን ሳይበክሉና የተፈጥሮን ሚዛን ሳይጋፉ ዘና ለማለት የሚያስችል ዘመናዊነትን የተላበሰ የአኗኗር ዘይቤ እየሆነ ነው።

ምክንያቱ ደግሞ አረንጓዴ ቱሪዝም አካባቢን ለመንከባከብና ለቀጣዩ ትውልድ ለማቆየት ትልቅ አዎንታዊ ሚና ይጫወታል። ሰዎች በዱር እንስሳት ጥበቃ ስፍራዎች፣ በብሔራዊ ፓርኮች እና በለመለሙ የአትክልት ቦታዎች ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ፣ ስለ ተፈጥሮ ያላቸው ግንዛቤና ፍቅር ይጨምራል። ይህም የቱሪስት መዳረሻዎች በፕላስቲክና በሌሎች ቆሻሻዎች እንዳይበከሉ፣ ዛፎች እንዳይቆረጡ እና የብዝሃ ሕይወት እንዲጠበቅ የሚያደርጉ አረንጓዴ አሠራሮችን እና ሕጎችን በስፋት ሥራ ላይ እንዲውሉ እያገዘ ይገኛል።

በተጨማሪም፣ ይህ በለመለመ አረንጓዴ ስፍራ ውስጥ የሚደረግ መዝናኛ ለሰው ልጅ ሁለንተናዊ ጤና የሚሰጠው ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ነው። ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተፈጥሮ መካከል ጊዜ ማሳለፍ ውጥረትን (Stress) ይቀንሳል፣ የደም ግፊትን ያስተካክላል፣ እንዲሁም የፈጠራ አቅምንና ደስታን ያሳድጋል። ዓለም መዝናኛን ከተፈጥሮ ጥበቃ ጋር አቀናጅቶ መጓዙ፣ ለሰው ልጅ ጤናማ ሕይወትም ሆነ ለፕላኔታችን ሕልውና ፍጹም ተመራጭና አማራጭ የሌለው ብልህ መንገድ መሆኑን እያረጋገጠ ነው። የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም በትናንትናው ዕለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከብሮ የዋለውን "የዓለም የአካባቢ ጥበቃ ቀን" መነሻ በማድረግ በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሠሩ እና እየተሠሩ ያሉ የአረንጓዴ ቱሪዝም መዳረሻዎች ለተዝናኖትና ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸውን ፋይዳ በተመለከተ ዳሰሳ አድርጓል፡፡


ፎቶ-ገፅ ድር
አዲስ አበባ ከተፈጥሮና አካባቢ ጋር የተስማሙ የመስህብ ስፍራዎችን እየገነባች ነው

## ጥቂት ስለ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ቀን

የዓለም የአካባቢ ጥበቃ ቀን በየዓመቱ ግንቦት 28 (እ.አ.አ June 5) የሚከበር ሲሆን፣ አከባበሩ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1972 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አዘጋጅነት ስቶክሆልም፣ ስዊድን በተካሄደው የሰው ልጅ አካባቢ ጉባኤ (Stockholm Conference on the Human Environment) ነው። ይህ ቀን በይፋ መከበር የጀመረው በፈረንጆቹ በ1974 ሲሆን፣ ዓላማውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአካባቢ ጥበቃ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና መንግሥታትና ግለሰቦች ለምድራችን ጤንነት አዎንታዊ ለውጥ እንዲያደርጉ ማነሳሳት ነው።

ቀኑ የሚከበርበት ዋነኛ ምክንያት በአካባቢያችን ላይ እየደረሱ ያሉ እንደ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የብዝሃ ሕይወት መመናመንና የብክለት ችግሮችን ወደ መድረክ ላይ በማምጣት መፍትሔ ለመፈለግ ነው። ይህም ቀን የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ እንድንጠቀም፣ የደን ጭፍጨፋን እንድንከላከልና ዘላቂ የአኗኗር ዘይቤን እንድንከተል የሚያስታውስ ነው። በአጠቃላይ፣ የዓለም የአካባቢ ጥበቃ ቀን እያንዳንዳችን ለምድር ደህንነት የምናበረክተውን ድርሻ እንድንገመግም እና የተሻለች ዓለምን ለቀጣዩ ትውልድ ለማቆየት ቃል የምንገባበት ወቅትና ዕለት ነው።

ዕለቱም "የአየር ንብረትንና የወደፊት ሕይወታችንን ለመጠበቅ በተፈጥሮ እንነሳሳለን" በሚል መርህ እየተከበረ ይገኛል፡፡

## ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተስማሙ የኢትዮጵያ ፕሮጀክቶች

የሰው ልጅ ታሪክ ከተፈጥሮ ጋር የተቆራኘ ነው። ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጅ መጠጊያ፣ ምግብ እና መረጋጋት ምንጭ የነበረችው ተፈጥሮ፣ በኢንዱስትሪ አብዮትና በዘመናዊ የከተሜነት መስፋፋት ሳቢያ ቀስ በቀስ እየራቅናት መጥተናል። በበርካታ ከተሞች እንደምንመለከተው ሁሉ፣ የከተማ ገጽታ በሲሚንቶ በተሞሉ ሕንጻዎችና በአስፋልት መንገዶች እየተተካ ነው። ይህ ሁኔታ ለልማት አስፈላጊ ቢሆንም፣ የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር የነበረውን ጥልቅ ቁርኝት በመሸርሸሩ የጤናና የሥነ-ልቦና ቀውሶችን እየፈጠረ መሆኑ በተደጋጋሚ ይነገራል፡፡ አሁን ላይ ዓለም አቀፋዊው የመዝናኛ ባህል ይህንን ጉድለት ለማስተካከል ወደ ተፈጥሮ እቅፍ እየተመለሰ ይገኛል። "አረንጓዴ መዝናኛ" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ፣ መዝናናትን ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በማጣመር የሰው ልጅን ሁለንተናዊ ጤና ለመጠበቅ የሚደረግ ብልህ እንቅስቃሴ እየሆነ ነው። በዚህ ረገድ ተጠቃሽ እየሆኑ ከመጡ ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡

በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች እየተከናወኑ ያሉት የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶችና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች፣ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ናቸው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለተፈጥሮም ተስማሚ በማድረግ ረገድ ለመዝናኛው ኢንዱስትሪ ትልቅ ለውጥ እያመጡ ይገኛሉ።

የከተማው መንገዶች በብስክሌትና በእግረኛ መሄጃ መንገዶች መታጀባቸው፣ እንዲሁም በየመንገዱ ዳር የሚተከሉት የተለያዩ የአበባና የዛፍ ዝርያዎች፣ የከተማዋን ገጽታ ከመቀየራቸውም በላይ ነዋሪው በአረንጓዴ እቅፍ ውስጥ እንዲዝናና ዕድል እየፈጠሩ ነው። ይህ የተፈጥሮንና የከተማን ውህደት በማምጣት በኩል ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ እየወሰደች ያለችው ፈር ቀዳጅ እርምጃ ነው።

በተለይም በኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶቹ ውስጥ የተካተቱት ዘመናዊ መናፈሻዎች፣ የወንዝ ዳር ፕሮጀክቶች፣ የሕዝብ መዝናኛ ስፍራዎች፣ ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው ንጹሕ አየር የሚተነፍሱባቸውና አካላዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉባቸው ማዕከላት ሆነዋል። እነዚህ ስፍራዎች የከተማውን የኮንክሪት ግርግር ሰብረው፣ ለሕፃናት፣ ለአረጋውያንና ለወጣቶች የተረጋጋ የሕይወት ተሞክሮን በመስጠት ረገድ የማይተካ ሚና እያበረከቱና የውጭ ጎብኚዎችንም እየሳቡ ነው፡፡

የቱሪዝም ጉዳዮች ከፍተኛ ተመራማሪና አማካሪ አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) በቅርቡ ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት ሐሳብ አዲስ አበባ ላይ የተሠሩ ፓርኮችና ሌሎችም የመዝናኛ ሥፍራዎች ቱሪስቶችን በመሳብ ረገድ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው አብራርተዋል። አረንጓዴ ፓርኮቹን ጨምሮ ታሪካዊ ሥፍራዎችና የጥበብ ማዕከላቱ ቱሪስቶች ለቀናት በከተማዋ እንዲቆዩ የማድረግ ትልቅ አቅም አላቸው፡፡

እነዚህ ከተፈጥሮ ጋር የተሳሰሩ ሥራዎች የኢትዮጵያን የመዝናኛ ባህል ከባህላዊው አኗኗር ወደ ዘመናዊና ሥነ-ምህዳሩን ወደማይጎዳ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሸጋገር እያደረጉት ነው። ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት እያሳየች ያለችው ይህ ተነሳሽነት፣ ለሌሎች ታዳጊ ሀገራት አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ መዝናኛ እንዴት የከተማ ኑሮ አካል ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ አርአያነት ያለው ተግባር ነው።

በእርግጥ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ መዝናኛ ልማት በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በአዲስ አበባ እንደ አራዳ ፓርክ፣ እንጦጦ ፓርክና ወዳጅነት አደባባይ ያሉ ዘመናዊ መናፈሻዎች ለከተማው ነዋሪ አዲስ የኑሮ ዘይቤን ፈጥረዋል። እነዚህ ስፍራዎች የከተማውን ግርግር ወደ ተፈጥሮ መረጋጋት በመቀየር፣ አረንጓዴ ልማት ለነዋሪዎች ጤና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አሳይተዋል።

ባሳለፍነው ማክሰኞ ዕለት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በይፋ ሥራ እንዲጀምር የተደረገው ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ያለው የመልሶ ማልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክትም በዚሁ ዐውድ የሚገለጽ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ ትልቅ ተነሳሽነት፤ የተራቆቱ አካባቢዎችን በዘመናዊ የአፈር ጥበቃ እና በወንዝ ማጣራት ወደ አረንጓዴ ስፍራዎች በመቀየር፣ የፍራፍሬ ፓርኮችን ከእግር ጉዞ እና ከብስክሌት መንገዶች ጋር በማቀናጀት መዲናችንን አድሷል ሲሉም በማኅበራዊ ሚዲያ የትስስር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአጠቃላይ 22 ነጥብ 25 ኪሎ ሜትር የወንዝ ዳርቻ ልማትን የሚሸፍነው ይህ ፕሮጀክት፤ የማይቆራረጥ የልማት ሥራችን ሕያው ምስክር ከመሆኑም በላይ የሀገራዊ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

**ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# የደም ግፊት መንስኤና የመቆጣጠሪ ዘዴዎች

- **በደም ግፊት መንስኤዎችና መፍትሔዎች ዙሪያ የሚስተዋለውን የግንዛቤ ክፍተት ተከታታይነት ባለው የማስገንዘቢያ ትምህርት መታገል ይገባል፤**

**በሽዋርካብሽ ቦጋለ**

በአሁኑ ወቅት የደም ግፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለልብ ህመም፣ ለስትሮክ እና ለድንገተኛ ሞት ዋነኛው መንስኤ በመሆን “ጸጥተኛው ገዳይ” የሚል መጠሪያን አትርፏል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን እያጠቃ የሚገኘው ይህ የጤና ቀውስ፣ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ይገኛል። የደም ግፊት በደም ስሮች ግድግዳ ላይ የሚያሳድረው ጫና የሰውነትን ጠቃሚ ክፍሎች ቀስ በቀስ በማዳከም ለከፋ የአካል ጉዳት የሚዳርግ ቢሆንም፣ ብዙዎች ግን ህመሙ ምንም ዓይነት የሚታይ ምልክት ስለማያሳይ በቸልተኝነት ሲያልፉት ይስተዋላል።

የደም ግፊት ህመም ካለባቸው ታካሚዎች መካከል አብዛኞቹ ለህክምና ባለሙያዎች ምክር የሚሰጡት ምላሽ እና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ተገዢነት እጅግ ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል። የአመጋገብ ስርዓትን ማስተካከል፣ አካላዊ እንቅስቃሴን ማዘውተር፣ ጨውና ቅባትን መቀነስ ለህክምናው ስኬታማነት ወሳኝ ቢሆኑም፣ በተግባር ግን የታካሚዎች ተነሳሽነት አናሳ መሆኑ ይስተዋላል። ይህ የግንዛቤ ክፍተትና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥን ተግባራዊ የማድረግ ዳተኝነት፣ ህክምናው ውጤታማ እንዳይሆን ከማድረጉም ባለፈ ለተወሳሰቡ የጤና እክሎችና ለከፍተኛ የህክምና ወጪ ይዳርጋል።

ይህንን ሰፊ የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ኮሌጆች ከመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ባለፈ፣ ወደ ማህበረሰቡ በመውረድ በተግባር ላይ የተመሰረቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎችና ተመራማሪዎች በታካሚዎች የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ጥናቶችን በማካሄድ፣ ውጤታማ የመገናኛ ስልቶችን መንደፍ ይኖርባቸዋል። የጤና ሳይንስ ተቋማት ከሚዲያ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ሳይንሳዊ መረጃዎችን በቀላል ቋንቋ ለህዝቡ ማድረስ የሚችሉበትን መድረክ በማመቻቸት፣ ጤናማ ትውልድ ለመፍጠር የበኩላቸውን ግዴታ መወጣት ይኖርባቸዋል።

በዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በነርሲግና ሚድ ዋይፈሪ ትምህርት ቤት ዲን የሆኑት መምህር ቢቂላ ተስፋ ኮሌጁ ከመማር ማስተማር በተጨማሪ ችግሩን የሚያቃልል የጥናትና ምርምር ስራዎችን እንደሚያካሄድ ገልፀው፣ በቅርቡ የደም ግፊት ታማሚዎች ዘንድ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ተገዢነትና ተያያዥ ሁኔታዎችን ለመለየት የተደረገው ጥናት የዚሁ አካል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ስር ባሉ ሆስፒታሎች (ዳግማዊ ምኒልክ፣ የካቲት 12፣ ራስ ደስታ፣ ጥሩነሽ ቤጂንግን ጨምሮ በስድስቱም ሆስፒታሎች) ክትትል በሚያደርጉ የደም ግፊት ታካሚዎች ዘንድ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ተገዢነት እና ተያያዥ ሁኔታዎች ላይ አተኩሮ በ2017 ዓ.ም በተካሄደው በዚህ ጥናት የደም ግፊት ህክምናና ክትትል የሚያደርጉ 415 ሰዎች ተካትተዋል፡፡ በጥናቱ ግኝትም የአኗኗር ዘይቤ ተገዥነት 29 ነጥብ 2 በመቶ መሆኑ ነው የተመላከተው፡፡ ይህ ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ያመላክታል፡፡



ፎቶ- ከፋይል
የአመጋገብ ስርዓትን በማስተካከልና የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በማዘውተር የደም ግፊትን መከላከል ይቻላል

እንደ መምህር ቢቂላ ገለፃ፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየጨመሩ ይገኛሉ። በተለይም በሰለጠኑ ሀገራት የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በስፋት ይታዩ የነበሩ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች አሁን ላይ በሀገራችንም በፍጥነት እየጨመሩ መጥተዋል፡፡

ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎችም ትልቁን ቦታ የሚይዘው የደም ግፊት በሽታ እንደሆነ ጠቁመው፣ በከተማም ሆነ በገጠር በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ መምጣቱን ያነሳሉ፡፡ በዓለም ላይም ቢሆን ከሚያጋጥመው የሞት ምክንያትና ውስብስብ የጤና እክሎች ትልቁን ቦታ የሚይዘው ከፍተኛ የደም ግፊት ነው ባይ ናቸው፡፡ ህመሙ በሰዎች ላይ የሚያስከትለው የስነ ልቦ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንደ መምህር ቢቂላ ገለፃ፣ ማንኛውም ሰው በተፈጥሮው ጤናማ የሆነ የደም ግፊት ሊኖረው ይገባል፡፡ ጤናማ የደም ግፊት የሚባው በደም ቧንቧ ውስጥ ደም ሲሰራጭ የሚፈጠር የደም ግፊት ሲሆን፣ ይህም ለሁሉም ሰው ሊኖረው የሚገባ ነው፡፡ ጤናማ ያልሆነ የደም ግፊት የሚከሰተው ደም በልብ አማካኝነት ወደተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ሲረጭ፣ በደም ቧንቧ ግድግዳዎች ላይ የሚፈጥረው ግፊት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ነው።

መደበኛው የደም ግፊት ከ120/80 mmHg በታች ሲሆን፣ ጤናማ ያልሆነ የደም ግፊት የሚባለው የላይኛው ቁጥር 140 እና ከዚያ በላይ፣ ወይም የታችኛው ቁጥር 90 እና ከዚያ በላይ ሲሆን። ይህ በሽታ ምልክት አልባነቱ፣ ሥር የሰደደ መሆኑና ውስብስብ ጉዳቶችን የሚያስከትል መሆኑ ከሌሎች በሽታዎች በተለየ አደገኛ ባህሪ እንዳለውና በአብዛኛው ሰው ላይ ግፊቱ በጣም እስኪጨምር ወይም የሰውነት አካላት ላይ ጉዳት እስኪያደርስ ድረስ ምንም አይነት የህመም ምልክት ላያሳይ ይችላል ብለዋል።

አንዴ የደም ግፊት ከተከሰተ በኋላ ታማሚው አብዛኛውን ጊዜ የረጅም ጊዜ ክትትልና የሕይወት ዘመን መድኃኒት ሊያስፈልገው እንደሚችል በትክክል ካልተቆጣጠሩት ግን ለልብ ድካም፣ ለስትሮክ (በድንገት የአካል ክፍል መስነፍ)፣ ለኩላሊት በሽታ እና ለዓይን እይታ ማጣት ዋና መንስኤ እንደሚሆን ነው።

ለደም ግፊት የሚያጋልጡ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በተለይ የእድሜ መጨመርና በቤተሰብ ውስጥ የደም ግፊት ታሪክ ካለ የመያዝ እድል የሚጨምር ሲሆን፣ በተለይ በአሁኑ ጊዜ እድሜና ፆታ ሳይለይ በአብዛኛው ሰው ላይ የሚታይ ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየበዙ የመጡት በተለይ በምግብ ውስጥ የጨው መጠን መብዛት፣ በፋሪካ የተቀነባበሩ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ፣ ጮማና ዘይት አብዝቶ መመገብ፣ ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አለማድረግ እንዲሁም ሲጋራና አልኮል በመጠቀም ነው።

ሌሎች ተጓዳኝ ህመሞችና ከልክ ያለፈ ጭንቀትም ለደም ግፊት ተጋላጭ የሚያርጉ ቢሆንም ህመሙን አስቀድሞ ለመከላከል ትልቁና ዋናው ነገር አመጋገብን ማስተካከልና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲሁም በቀን ለ30 ደቂቃ በእግር ፈጠን ብሎ በመጓዝ ህመሙን አስቀድሞ መከላከል ያስችላል፡፡

ከዚህም ሌላ የጨው አጠቃቀምን መቀነስ፤ ለምሳሌ በቀን ከአንድ የሻይ ማንኪያ በታች መጠቀም፣ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ በፖታሲየም የበለፀጉ ምግቦችን አዘውትሮ ከመመገብ በተጨማ ምልክት ባይኖርም እንኳ በየጊዜው ደም ግፊት የመለካት ወይም መደበኛ ምርመራ ማድረግም ለመከላከል ያስችላል።

ሲጋራ አለማጨስና የአልኮል መጠጦችን መጠጥን መቀነስ ወይም ጨርሶ ማቆም፣ ጭንቀትን በመቀነስ በቂ እረፍት ማድረግ፣ በቂ እንቅልፍ ማግኘት እና ዘና የሚያደርጉ ነገሮችን ማድረግ ለደም ግፊት ቁጥጥር ወሳኝ ነው ባይ ናቸው፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ ግፊቱ የተስተካከለ ቢመስልም እንኳ ያለ ሀኪም ትዕዛዝ በፍጹም መድሐኒት አለማቋረጥ ብሎም በቤት ውስጥ ወይም በጤና ተቋም የደም ግፊትን በመደበኛነት መለካት እንደሚገባም ነው የመከሩት፡፡

በጥናቱ መሰረት የአኗኗር ዘይቤ ተገዥነት 29 ነጥብ 2 በመቶ ወይም ዝቅተኛ ስለመሆኑም እንደምክንያት ያስቀመጡትም በጉዳዩ ዙሪያ ማህበረሰቡ ያለው እውቀትና ግንዛቤ ወደ 46 በመቶ መሆኑን ይህም ሰፊ የሆነ የግንዛቤ እጥረት መኖሩን ሚያመላክት ነው፡፡ መድሐኒት በመውሰድ ብቻ የደም ግፊት ህመምን መከላከል እንደማይቻል ይልቁንም ከላይ የተጠቀሱትን የመከላከያ መንገዶችን መተግበር በእጅጉን ይገባል ብለዋል፡፡

የደም ግፊትን ጨምሮ ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመከላከል ህብረተሰቡ ብቻም ሳይሆን በየደረጃው ያሉ የህክምና ተቋማት ባለሙያዎች ማከም ብቻ ሳይሆን ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን መስጠት፣ በጤና ቢሮ ጠዋት ጠዋት የሚሰጡ የጤና ትምህርቶች መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ትምህርት እንዲሰጥ አቅጣጫና መመሪያ በማውረድ ግንዛቤውን ማስፋት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# ልጆች ለፈተናው እንዴት እየተዘጋጃችሁ ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በአዲስ ብርሃን ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ተፈታኞች በመፃህፍት ቤታቸው የፈተና ዝግጅት ሲያደርጉ

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ፤ በተለይም የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና እና የ8ኛ ክፍል የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ተፈታኞች፤ ለፈተና እየተዘጋጃችሁ ነው አይደል? ጎበዞች፡፡ የዛሬ ርዕሰ ጉዳያችን እያደረጋችሁት ስላለው የፈተና ዝግጅት ነው፡፡ ተፈታኝ ልጆችም ለፈተናው እየተዘጋጁ ያሉበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል አናግረን ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡

ሜሮን ይግረም እባላለሁ፡፡ በአዲስ ብርሃን ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ በዘንድሮው ዓመትም የ8ኛ ክፍል የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ከተማ አቀፍ ፈተና እየተዘጋጀሁ ነው፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ስለተፈተንኩ ለእኔ አዲስ አይደለም፡፡

በተለይም ከጓደኞቼ ጋር የቀደሙ ፈተናዎችን በጋራ በመስራት ላይ እገኛለሁ፡፡

ጌታው ሰለሞን እባላለሁ፡፡ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ የምማረው በአዲስ ብርሃን ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የ6ኛ ክፍል ሚኒስትሪ ፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ጥናት የጀመርኩት ቀደም ብዬ ነው፡፡ በትምህርት ቤት የሚሰጠውን መደበኛ እና የማጠናከሪያ ትምህርት በአግባቡ ተከታትያለሁ፡፡ ከዚህ በፊት የተሰሩ የ6ኛ ክፍል ሚኒስትሪ ፈተናን እና በትምህርት ቤቱ የሚሰጠውን የፈተና ጥያቄዎች እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡

አንዷለም ተሾመ እባላለሁ፡፡ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ለፈተና ዝግጁ መሆን አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በትምህርት ቤታችን በየሳምንቱ ቅዳሜ የሚሰጡንን የማጠናከሪያ ትምህርቶችን እየተማርኩ ነበር፡፡ የቆዩ የፈተና ጥያቄዎች በግሌም ሆነ ከጓደኞቼ ጋር እየሰራን ነው፡፡ የትምህርት ክፍለ ጊዜዬን ስጨርስ በትምህርት ቤቱ ቤተ መፃህፍት በመገኘት አነባለሁ፡፡ ጓደኞቼ ጋር በትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ በጋራ ጥያቄ እያወጣን እንጠያየቃለን፣ ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀልንን ጥያቄዎችንም በጋራ እንሰራለን፡፡

ኤደን አሰበ እባላለሁ፡፡ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ለሚኒስትሪ ፈተና እየተዘጋጀሁ እገኛለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው ክፍል ውስጥ ትምህርት ሲሰጥ በመከታተል ነው፡፡ የተማርኩትንም ድጋሜ አነባለሁ፡፡ ስማር ወይም ሳነብ ያልገባኝ ነገር ሲኖር በግሌ መምህራንን እጠይቃለሁ፡፡ ከዚህ በፊት በጨዋታ የማሳልፋቸውንም ጊዜያት ጭምር ለንባብ አውላለሁ፡፡

ቤተሰቦቼም ውጤታማ እንድሆን ያበረታቱኛል፡፡ የስራና የጥናት ሰዓት በሚልም ፕሮግራም አውጥቼ አነባለሁ።፡ ጥሩ ውጤት እንደማመጣም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ልጆች እንዴት ናችሁ ተሰማ መንግስቱ እባላለሁ፡፡ የአዲስ ብርሃን ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ነኝ፡፡ የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና እና የ8ኛ ክፍል የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ፈተናን ጥሩ ውጤት አምጥታችሁ እንድታልፉ ጠንክራችሁ ማንበብ እንዳለባችሁ እንዳትዘነጉ፡፡

ልጆች፤ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ለማንበብ መሞከር አዕምሮን ስለሚያጨናንቅ ዕቅድ በማውጣት አንብቡ፡፡ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ እየያዛችሁ ማንበብ፣ ከዚህ ቀደም የተሰጡ ፈተናዎችን በመስራት እና በመለማመድ መዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

ክፍለ ጊዜያችሁን ያለምንም መሸራረፍ በመጠቀም፣ መምህራን የሚሰጡትን የማጠናከሪያ ትምህርት በመከታተል፣ ከመደበኛው ትምህርት ጊዜ ውጭ የእረፍት ቀናትን እንዲሁም ማታ የተማራችሁትን በማንበብ ለጥሩ ውጤት ተዘጋጁ፡፡

ከዚህ ባለፈም የተማሪ መታወቂያችሁን በማስያዝ ከቤተ መፃሕፍት ተውሳችሁ ማንበብም ትችላላችሁ፡፡ በዚህ ልክ ጠንክራችሁ ካነበባችሁ በዘንድሮ ፈተናም ጥሩ ውጤት እንደምታመጡ በልበ ሙሉነት እነግራችኋለሁ፡፡

ልጆች ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋችኋል፡፡ ጥሩ ውጤትም ታመጣላችሁ፡፡ ለወደፊትም ልታሳኩት ወደፈለጋችሁበት እንድትደርሱ ይረዳችኋል፡፡ መልካም ፈተና እንዲሆንላችሁ እመኛላችኋለሁ፡፡

## የቁርጡሚ ወንዝ አዲስ መልክ!



ውድ ልጆች! በአዲስ አበባ ከተማችን ውስጥ የሚገኘው የቁርጡሚ ወንዝ ስያሜውን ያገኘው ከአፋን ኦሮሞ ሲሆን ትርጉሙም ዓሣ ማለት ነው። ወንዙ በጥንት ዘመን እጅግ ንፁህና ያልተበከለ ስለነበር፣ በርካታ ዓሣዎች በውስጡ በነፃነት ይዋኙበት ነበር። ይህ አስደናቂ ወንዝ መነሻውን ከእንጦጦ ተራራማ ሥፍራዎች በማድረግ ጉዞውን ይጀምራል። ከዚያም ባንተይቀጡ ከሚባለው ወንዝ ጋር አንድ ላይ በመሆን በመጨረሻ ከታላቁ አቃቂ ወንዝ ጋር ሙሉ በሙሉ ይቀላቀላል።

ይሁን እንጂ የከተማችን ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ፣ ከተለያዩ ቤቶችና ፋብሪካዎች የሚለቀቁ ቆሻሻዎች የወንዙን ንፅህና አጠፉት። ለብዙ ዓመታትም የቆሻሻ መከማቻ በመሆኑ ለጤና አስጊ የበሽታ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል።

በአሁኑ ወቅት ግን በኮሪደር እና በወንዞች ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት አማካኝነት ወንዙን የመንከባከብ ሥራ በስፋት እየተሰራ ነው። አሁን የቁርጡሚ ወንዝ ከነበረበት የብክለት አደጋ ወጥቶ ታድሷል። እኛም ይህንን ውብና ሳቢ የመዝናኛ ስፍራ ሁልጊዜ በንፅህና የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን!

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**አንዷት ግንድ በሁለት ትከሻ ትጓደድ**

**መልስ፡-** ሐ. ቀንበር

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ስትጮህ ስነካት ወሬ የምታወራ ምንድን ናት?**

ሀ. ቆርቆሮ

ለ. ሞባይል ስልክ

ሐ. ከበሮ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

# የቅጥር ማስታወቂያ

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለቋንቋዎች ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | ትግርኛ ቋንቋ ጀማሪ ሪፖርተር | VII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 0 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.735 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 2 | ትግርኛ ቋንቋ ሪፖርተር | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.730 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 3 | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.802 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ በድጋሚ የወጣ |
| **የዲጂታል ሚዲያና ህትመት ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 4 | የዲጂታል ይዘት ፕሮዳክሽን ዝግጅት እና ስርጭት ዲፓርትመንት ኃላፊ | XV | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 10/8 ከዚህ ውስጥ በም/ዋና አዘጋጅነት 2 ዓመት የሰራ/ች | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.1112 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 5 | ከፍተኛ የግራፊክስና አኒሜሽን ባለሙያ (ለህትመት ዝግጅት ክፍል) | XIII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤም.ኤስ.ሲ | 8/6/4 ዓመት | ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮምፒውተር አፕሊኬሽን፣ ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ፣ ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ ሲነማቶግራፊ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.303 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 6 | የካሜራ ባለሙያ | IX | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤስ.ሲ | 4/2 ዓመት | በፎቶግራፍ፣ ቪዲዮግራፊና በሲኒማቶግራፊ፣ በኤሌክትሪክሲቲ፣ ICT, Film Directing በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኮምፒውተር ሳይንስ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.310 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| **የሀብት አስተዳደር ዘርፍ (በድጋሚ የወጣ)** | | | | | | | | | | |
| 7 | ሜካፕ አርቲስትና አልባሳት ተቆጣጣሪ | VIII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤ ዲግሪ | 4/2 ዓመት | በስነ ጥበብና ዲዛይን ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.875 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| **ለዋና ስራ አስፈፃሚ ጽህፈት ቤት ስር ላሉ ዳይሬክቶሬቶች (በድጋሚ የወጣ)** | | | | | | | | | | |
| 8 | ከፍተኛ የለውጥ ስራዎች ትግበራና ክትትል ባለሙያ | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በሥራ አመራር፣ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን | አ/18.027 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| **ለቴሌቪዥን ዘርፍ (በታለንት ግዜ)** | | | | | | | | | | |
| 9 | የቴሌቪዥን የመዝናኛ ዝግጅቶች እና ለአዲስ ታለንት ሾው ዝግጅት የዝግጅት አስተባባሪ | - | በማንኛውም የትምህርት ዝግጅትና ደረጃ ሆኖ በቴሌቪዥን መዝናኛ ላይ ልዩ ችሎታ እና ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች | በዘርፉ ልምድና ክሎት ያላችሁ እንዲሁም ሞዴል አርትስቶች ጭምር መሳተፍ ይችላሉ | • የተለያየ የቴሌቪዥን መዝናኛ ዝግጅቶችን እና ፊውቸር ፊልሞችን በማስተባበር ልምድ ያለው ወይም ያላት። • የኮምኒኬሽን እና ማርኬቲንግ ክህሎት ያለው ወይም ያላት • መሰረታዊ የሙዚቃ ክህሎት ያለው/ያላት • የካሜራ ዳይሬክቲንግ ክህሎት ያለው ወይም ያላት። | - | እንደ አስፈላጊነቱ | በታለንት ግዚ | በተቋሙ አሰራር እና ስምምነት | አ/አ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ እና የፋይዳ መታወቂያ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ለትግረኛ ጀማሪ ሪፖርተርና ሪፖርተር ላይ የምትወዳደሩ በመዝናኛ ላይ ልምድ እና ተሰጥዖ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል
6. የምዝገባው ቀን ከሰኔ 01 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ሰኔ 12 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
7. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
8. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በቴክኖሎጂ የታገዘ የከተማ ግብርና

- በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከ3 ሺህ በላይ የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እየተገበሩ ነው፤

**በይግለጡ ጓዴ**

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ እንደ ሲንጋፖር እና ቶኪዮ ያሉ ከተሞች አፈር-አልባ የሃይድሮፖኒክስ ቴክኖሎጂን፣ አቀባዊ እርሻን (Vertical Farming) እና የአየር ንብረትን በኮምፒውተር የሚቆጣጠሩ ዘመናዊ ግሪን ሃውሶችን (አረንጓዴ መጠለያዎች) በስፋት እየተጠቀሙ ይገኛሉ። እነዚህ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎች በመተግበራቸው የቦታ እጥረትን በመቅረፍ ምርታማነትን እስከ አስር እጥፍ ማሳደግ የተቻለ ሲሆን፣ የውሃ ብክነትን እስከ 90 በመቶ መቀነስና ዓመቱን ሙሉ ያለምንም የአየር ንብረት ተጽዕኖ የግብርና ምርትን ለከተማው ማህበረሰብ ማቅረብ ተችሏል። ይህም ከተሞቹ በምግብ ራስን ከመቻል ባለፈ የካርቦን ልቀትን በመቀነስ ረገድ አስደናቂ ውጤት እንዲያስመዘግቡ አስችሏቸዋል።

ይህ የዓለም ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር እየታዩ ያሉትን የከተማ ግብርና ስኬቶች ይበልጥ ለማሳደግና የነዋሪውን የምግብ ዋስትና በዘላቂነት ለማረጋገጥ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች አሁን ካሉበት አቅም በበለጠ እና በተቀናጀ መልኩ መጠቀም ያስፈልጋል። በተለይም በከተማዋ ያለውን የተወሰነ የቦታ አማራጭ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ወጣቶችና ሴቶች በየመኖሪያ መንደራቸው በትንሽ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት ሊያስገኝ በሚችለው የአቀባዊ እርሻ እና የጠብታ መስኖ ስልቶች ላይ በስፋት እንዲሰማሩ ማገዝ የከተማዋን የምርት ፍላጎት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሙላት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

ስለሆነም አዲስ አበባ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ በጀመረችው ጉዞ፣ እነዚህን የቴክኖሎጂ አማራጮች ከቀላል የጓሮ አትክልት ልማት ባለፈ በትላልቅ ተቋማት፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች ሰገነት እና በክላስተር በተደራጁ ማህበራት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ልትተገብራቸው ይገባል። መንግስት እና የግሉ ዘርፍ በጋራ በመሆን የቴክኖሎጂ አቅርቦትንና የስልጠና ድጋፎችን ተደራሽ ማድረግ ከቻሉ፣ የከተማዋ የግብርና ዘርፍ የነዋሪዎቿን የዕለት ተዕለት የምግብ ፍላጎት ከመሸፈንም በላይ ለአረንጓዴና ዘመናዊ ከተማ መገንባት አይነተኛ ምሰሶ መሆን ይችላል።

በሀገራችን ያለው ግብርና በአብዛኛው በአነስተኛና በተበታተኑ ማሳዎች ላይ የሚካሄድ በመሆኑ፣ የምርትና ምርታማነት እድገቱ ከተጠቃሚው ፍላጎት ጋር ሲነፃፀር አሁንም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ አይነቱ የተበታተነ ይዞታ አርሶ አደሩ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ግብዓቶችን በአግባቡ እንዳይጠቀም ማዕቀብ ከመሆኑም በላይ፣ ምርቱ በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆን አድርጎታል።



ፎቶ- ከገፀ ድር
የከተማ ግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ ልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በጥቅም ላይ ውለዋል

ይሁን እንጂ እነዚህን ይዞታዎች በማሰባሰብና በማዋሃድ መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎችን መፍጠር፣ እንዲሁም የከተማ ግብርናን በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መደገፍ ለችግሩ ቁልፍ መፍትሔ እየሆነ መጥቷል። የከተማ ግብርና በአነስተኛ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት፣ ጥራትና ፍጥነትን በማረጋገጥ የከተማውን ማህበረሰብ የስራ እድል፣ የምግብ ዋስትና እና አረንጓዴ አካባቢ ተጠቃሚነት እያጠናከረ ይገኛል።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት፣ የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ አራት ዋና ዋና የቴክኖሎጂ አማራጮች ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው፡፡ አንደኛው አፈርን በአግባቡ በማይፈልግ መልኩ፣ ተክሎች ለዕድገታቸው የሚያስፈልጋቸውን ማዕድን በውሃ ብቻ እንዲያገኙ የሚያደርግ ዘመናዊ የልማት ዘዴ (ሃይድሮፖኒክስ) ነው። ሁለተኛው አኳፖኒክስ ሲሆን፣ ይህም የዓሣ እና የአትክልት ልማትን የሚያስተሳስር ዘላቂ ዑደት ነው። የዓሣው ቆሻሻ ለተክሎች ማዳበሪያነት ሲያገለግል፣ ተክሎቹ ደግሞ ውሃውን አጣርተው ለዓሣዎቹ ንጹህ አካባቢ ይፈጥራሉ። በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው አቀባዊ እርሻ ነው፡፡ ይህም ሰብሎችን በተደራረቡ መደርደሪያዎች ላይ በማልማት፣ በአነስተኛ የቦታ ስፋት ላይ እጅግ ከፍተኛ ምርት ማግኘት የሚያስችል ዘዴ ነው። አራተኛውና የመጨረሻው አውቶሜትድ የመስኖ ስርዓት ሲሆን፣ የተክሎችን እርጥበት፣ የሙቀት መጠን እና ሌሎች ሁኔታዎችን በሴንሰሮች በመቆጣጠር ውሃን በቁጠባና በብቃት መጠቀም የሚያስችል አሰራር ነው።

በከተማ ዙሪያና መሃል የሚመረቱ አትክልትና ፍራፍሬዎች ረጅም ርቀት ሳይጓዙ በፍጥነት ለተጠቃሚው ስለሚደርሱ ጥራታቸውና ቫይታሚናቸው ሳይቀነስ ትኩስ ምግብ ለማግኘት ያስችላሉ። ይህም የኑሮ ውድነትን ከመቀነሱም በላይ ማህበረሰቡ በራሱ ግቢ ወይም ሰገነት ላይ በማምረት የገበያ ወጪውን እንዲቆጥብ ያደርጋል። በተለይም ለወጣቶች እና ለሴቶች እንደ ግሪን ሃውስ አስተዳደር እና ምርት ማቀነባበር ባሉ ስራዎች ሰፊ የገቢ ምንጭ እየፈጠረ ይገኛል። ከዚህም ባሻገር የከተማን ሙቀት መጠን በመጠኑ ጠብቆ ማቆየት፣ የካርቦን ልቀትን መቀነስ እና ብክነትን ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያነት በመቀየር ረገድ የአካባቢ ጥበቃ ሚናው ከፍተኛ ነው።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የሰብል ልማት ቡድን መሪ አቶ ጉደታ ሽብሩ እንደገለጹት፣ ክፍለ ከተማው የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት ዘለቄታ ያላቸው የቴክኖሎጂ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል። ጽህፈት ቤቱ በበጋ መስኖ ስራ ላይ ለአርሶ አደሮች የውሃ መሳቢያ ጀነሬተሮችን በድጋፍ ያበረከተ ሲሆን፣ አርሶ አደሮቹ በሜካናይዜሽን ታግዘው በጋራም ሆነ በግል በትራክተር እንዲያርሱ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ሰርቷል። ባለሙያዎች በመስክ በመገኘት የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ እየሰጡ ሲሆን፣ ለክረምቱ የእርሻ ስራ የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ቅድመ-ልየታ ተደርጎላቸዋል።

“በአሁኑ ወቅት በክፍለ ከተማችን 525 አርሶ አደሮች ማሳቸው ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርታማነትን ለማሳደግ እየሰሩ ይገኛሉ። አርሶ አደሮቹ በዘር ወቅት የምርጥ ዘር ግብዓቶችን በባለሙያ እገዛ በማሳ ላይ በመስመርና በክላስተር እንዲዘሩ በተግባር የታገዘ ስልጠና ሰጥተናል”

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእጽዋት ልማት ቡድን መሪ ወይዘሮ ታየች አለማር በበኩላቸው፣ በክፍለ ከተማው ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ገልጸዋል። በዚህም መሰረት 52 የውሃ መሳቢያ ሞተሮች፣ 4 የጠብታ መስኖዎች፣ 3 የሃይድሮፖኒክስ ቴክኖሎጂዎች እና 1 ትራክተር ለአገልግሎት ውለዋል። በተጨማሪም በመንግስት በኩል ለቤተሰብ ፍጆታ የሚሆን 103 ኪሎ ግራም እና በማሳ ደረጃ በግል ለሚያመርቱ 42 ኪሎ ግራም የአትክልት ዘር ቀርቧል።

ወይዘሮ ታየች እንዳሉት፣ ማህበረሰቡ በአብዛኛው ለምግብ ፍጆታ ማምረትን የለመደ ሲሆን አርሶ አደሮችም ያላቸውን አቅም አሟጠው ውሃ በማስቆፈርና 2 እና 3 ሞተሮችን በመጠቀም ክረምትን ሳይጠብቁ በዓመት እስከ 2 እና 3 ጊዜ ማምረት ችለዋል። ይህ አሰራር አርሶ አደሮቹ ገበያ መር አመራረትን እንዲከተሉና ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉ ረድቷቸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የከተማ ግብርና ግብዓት እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት አመቻች ቡድን መሪ አቶ ኢሳያስ አበበ፣ በከተማዋ የሰብል ምርትን ለማሳደግ የጠብታ መስኖ፣ ሃይድሮፖኒክስ፣ በነዳጅና በሶላር (በፀሐይ ኃይል) የሚሰሩ የውሃ መሳቢያ ጀነሬተሮች፣ የኤሌክትሪክ ፓምፖች እንዲሁም የቢቢኤም (BBM) ማረሻ ማጠንፈፊያ ቴክኖሎጂዎች በተቋማትና በግለሰብ ደረጃ ጥቅም ላይ መዋላቸውን አረጋግጠዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከባዮጋዝ (Biogas) ማመንጫዎች በኋላ የሚወጣውን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ አርሶ አደሮች ወስደው እንዲጠቀሙበት እየተደረገ ይገኛል።

እንደ አቶ ኢሳያስ ገለጻ፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም ምርትን ከመጨመር ባለፈ ጥራትን ያረጋግጣል። በአፈር አልባ (ሃይድሮፖኒክስ) ቴክኖሎጂ የሚመረት ምርት ለተመጣጣኝ ምግብ ፍጆታነት ከመዋሉም በላይ ለገበያ ቀርቦ ከፍተኛ ገቢ ያስገኛል።

በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከ3 ሺህ በላይ የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እየተገበሩ ይገኛሉ። በቀጣይም መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ይህንን የቴክኖሎጂ እና የግብዓት ድጋፍ አጠናክረው ከቀጠሉ፣ የከተማ ግብርና የከተማዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የነዋሪዎቿን ህይወት ለመቀየር ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ አያጠራጥርም።

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# ከስጋትነት ወደ ኢንዱስትሪ ስፍራነት

- **ባለፉት አስር ወራት 27 ነጥብ 2 ሄክታር ማዕድን የሚወጣበት መሬት መልሶ እንዲለማ ተደርጓል፤**

**በለይላ መሀመድ**

በተንጣለለው ሜዳ ላይ የከተመው የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ በዘመናዊ መልኩ ለምቷል፡፡ የፓርኩ ቅጥር ግቢም ሆነ ዙሪያ ገባው በአረንጓዴ ልማት ተውቧል፡፡ ከለማው የአረንጓዴ አካባቢ የሚነፍሰው ንፁህ አየር ሞቃታማውን የአየር ጠባይ አቀዝቅዞታል፡፡ የፓርኩ አጠቃላይ ገፅታ ለእይታ ምቾት ይሰጣል፤ መንፈስንና አካልን ያድሳል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኮንስትራክሽን ማዕድን ወጥቶበት በመልሶ ማልማት የለማው የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ መንደር

የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሽዋፈራሁ ኃይለጊዮርጊስ አካባቢው ከመልማቱ በፊት የነበረበትን ገፅታ ያስታውሱታል። የኢንዱስትሪ ፓርኩ ከመልማቱ በፊት ስፍራው ገደላማና ምድረ በዳ እንደነበር ይገልጻሉ። “ለሰውና ለእንስሳት ስጋት የነበረ ስፍራም ነበር፡፡ አሁን ግን በጣም በአማረ ሁኔታ ለምቷል፡፡ በርካታ ህንጻዎች ተሰርተውበታል፡፡ ለእኛም የስራ እድል ፈጥሮልናል” ሲሉም ይናገራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ የግንባታ (የኮንስትራክሽን) ማዕድን የወጣባቸውን ስፍራዎች በመልሶ ማልማት ዳግም ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ በማድረግ ረገድ የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ የመልሶ ማልማት የተከናወነባቸው የኮንስትራክሽን ማዕድን የወጣባቸውን ስፍራዎችን በማልማት ተግባር ውስጥ የመጣው ውጤት ምን እንደሚመስል በማሳያነት ከተጠቀሱት መካከል አንዱ ነው፤ የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ፡፡

በስፍራው ተገኝተው የኢንዱስትሪ ፓርኩ ከመልማቱ በፊት ስለነበረበት ነባራዊ ሁኔታ ገለጻ ያደረጉልን በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ ምህዳር ብዝሀ ሕይወት ቁጥጥርና የመልሶ ማልማት ባለሙያ ወይዘሮ ውድነሽ መንግስቱ ናቸው፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የኮንስትራክሽን ማዕድን ልማት ለሀገሪቱ የከተሞች እድገትና የመሰረተ ልማት ግንባታ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ ሸክላ እና ጂፕሰም ያሉ ግብዓቶችን የሚያቀርብ ወሳኝ ዘርፍ ነው። በኢትዮጵያ ይህ ዘርፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ፍላጎት በማሟላት፣ የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት እና በርካታ የስራ እድሎችን በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ማዕድኑ ከወጣ በኋላ የኮንስትራክሽን ማዕድን መልሶ ማልማት ደግሞ ሌላው ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ በኮንስትራክሽን ማዕድን ልማት መልሶ ማልማት ማለት የተለያየ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ወጥቶ ያለቀበትን ቦታ ተመልሶ ወደነበረበት ይዞታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ማስተር ፕላን መሰረት አካባቢው የኢንዱስትሪ ፓርክ ስለነበር፣ ይህ የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመልሶ ማልማት ሊለማ ችሏል። አሁን ላይ አካባቢው በሥነ ምህዳር የተዋበና የለማ ሆኗል፡፡ መልሶ ማልማት ያስፈለገበት ዋና ዓላማም የአደጋ ስጋት የነበረውን ቦታ ወደ ቀደመ ይዞታው መመለስ ሲሆን፣ አልፎ ተርፎም በዚህ ደረጃ ለሀገር ኢኮኖሚ ማደግ ሁነኛ አስተዋጽኦ ወደሚያበረክት ልማት መለወጥ ነው፡፡ በ93 ነጥብ 9 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ዘመናዊው የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዘመናዊ መሠረተ ልማትን ከውጤታማ ቴክኖሎጂ አሰናስሎ የተገነባ አስደናቂ ፕሮጀክት ነው። ዙሪያውም በአረንጓዴ ልማት ተውቧል፡፡

የዝግጅት ክፍሉ በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሥርዓተ ምህዳርና ብዝሀ ሕይወት አያያዝ ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ይታገሱን አነጋግሯቸዋል፡፡ እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በመሰረታዊነት የኮንስትራክሽን ማዕድን ከወጣ በኋላ የተቆፈረው መሬት ይሞላል፡፡ እንደየ አስፈላጊነቱ ለታለመለት ዓላማ ይውላል።፡ የመልሶ ማልማት ስራው በዋናነት ሶስት መሰረታዊ እቅዶችን ለማሳካት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ነው። መልሶ ማልማት ማለት በኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሂደት ውስጥ የተጎዱ መሬቶችን በከተማዋ መሪ ማስተር ፕላን መሰረት ለሚቀጥለው የልማት ተግባር መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

የከተማዋ መሪ ማስተር ፕላን ለግብርና ስራ፣ ለአረንጓዴ ልማት፣ ለመሰረተ ልማትና ለግንባታ ስራዎች የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የኮንስትራክሽን ማዕድን ለማውጣት የተቆፈሩ ቦታዎችን መሪ ማስተር ፕላኑን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲያለሙ በማድረግ ረገድ ለሚቀጥለው የልማት ስራ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ማዕድን ማውጣት በባህሪው ቁፋሮን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ አንድ ማዕድን የወጣበት ስፍራ ቀደም ሲል የነበረውን ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ወይንም ቅርጽ ይቀይራል፤ ጉድጓድ ይፈጠራል፡፡ ጉድጓዱ በወቅቱ ካልለማ ለአደጋ ስጋት ይሆናል፡፡ ተፈጥሯዊ መልክአ ምድሩም ተቀይሮ ለእይታም ጭምር አያስደስትም። ከዚህ አንጻር መልሶ መልማትና ለታለመለት ልማት መዋል ይኖርበታል፡፡

ዳይሬክተሩ አያይዘውም፤ መልሶ ማልማት በሶስት አይነት መንገድ ይከናወናል፡፡ ማዕድን የወጣበት ቦታ ለመንገድ፣ ለቤት ግንባታና ለሌሎች መሰረተ ልማት ስራዎች እንዲውል ታስቦ የሚሰራ የመልሶ ማልማት ስራ ከሆነ ጉድጓዱን የመድፈንና የመደልደል ስራ ብቻ ይሰራል፡፡ ለግብርና ልማት ስራ የሚውል ቦታ ከሆነ ደግሞ ከመሙላትና ከመደልደል ባለፈ ከላይ የለማ አፈር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተክሉ ወይም ሰብሉ የሚፈልገውን ንጥረ ነገር ከአፈሩ ማግኘት ስለሚኖርበት፣ በግዴታ ለግብርና ስራ የሚውል የአፈር አይነት እንዲሞላ ይደረጋል፡፡ በማስተር ፕላኑ መሰረት ቦታው ለአረንጓዴ ልማት የሚውል ከሆነ፣ ቅድሚያ የጎደጎደውን ቦታ የመሙላትና የመደልደል ስራ ከተሰራ በኋላ ልክ እንደ ግብርናው በለማ አፈር እንዲሞላ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ይህ አሰራር በአረንጓዴ ልማት ስራው የሚተከሉ እጽዋት እንዲጸድቁ ያደርጋቸዋል፡፡

መልሶ ማልማት የተሰራባቸው ቦታዎች አደጋ በማያደርስ ደረጃ ላይ ከመሆናቸውም ባለፈ፣ የመሬትን ተፈጥሯዊ ጉዳት በመቀነስ የአካባቢው ሥነ ምህዳር እንዲጠበቅ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም ከተማዋን ወደ ዑደታዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት አቅጣጫ በማምራት ዘላቂ የከተማ ልማት እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ የመጀመሪያው ጥቅሙ የኮንስትራክሽን ማዕድኑን ለተለያዩ የልማት ስራዎች ማዋል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በመልሶ ማልማት ሀገራዊ ጥቅም የሚሰጡ የልማት ስራዎችን መስራት መቻሉ ነው፡፡ ይህም እንደ መልካም አጋጣሚ ይወሰዳል፡፡

የኮንስትራክሽን ማዕድን ከወጣባቸው በኋላ የመልሶ ማልማት ተሰርቶባቸው አሁን ለተለያዩ የልማት ስራዎች የዋሉ በርካታ አካባቢዎች ላይ ግዙፍ ተቋማት ተገንብተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በቦሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ የቂሊንጦ የመድኃኒት ፋብሪካ እንዲሁም በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተመረቀው የገላን ጉራ ኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ወስደው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ በማዕድን ማልማት ስራ ውስጥ የተሰማሩ 187 የኮንስትራክሽን ማዕድን አልሚዎች አሉ፡፡ ባለስልጣኑ በተያዘው በጀት ዓመት 30 ሄክታር መሬት ላይ በአልሚዎች የመልሶ ማልማት ስራ እንዲሰራ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል በሚል በእቅድ የያዘ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም 27 ነጥብ 2 ሄክታር መሬት በበጀት ዓመቱ 10 ወራት ውስጥ የመልሶ ማልማት ስራው ተከናውኗል፡፡

የተሰራው ስራ ካለው አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲወዳደር በቂ አለመሆኑን ዳይሬክተሩ አንስተው፤ ይህንን ለማስተካከል ከአልሚዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት መግባባት ላይ በመደረሱ፣ ወደ ተግባር ያልገቡ አልሚዎች በፍጥነት ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ መልሶ ማልማት የተካሄደባቸው አካባቢዎች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከአደጋ ስጋት ነጻ የሆነ ቀጣና ተፈጥሯል፡፡ ቀደም ሲል በአብዛኛው ማዕድን የወጣባቸው ስፍራዎች በፍጥነት የመልሶ ማልማት ስራ ስለማይሰራባቸው በክረምት ወቅት ውሃ ይቋጥሩ ነበር፤ በዚህም ልጆች “እንዋኝ” በሚል ሕይወታቸውን የሚያጡበት አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ እንስሳትም ለአደጋ ይጋለጡ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ይህ ችግር ቀንሷል፡፡

የመልሶ ማልማት ስራ የአካባቢን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ፣ እንዲሁም አካባቢያዊ የልማትና የከተማዋን እድገት ለማፋጠን ከፍተኛ አበርክቶ እንዳለው አልሚዎች ተረድተው በቀጣይም በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ዳይሬክተሩ አመላክተዋል፡፡

## እንጆሪ... ከገጽ 6 የዞረ

የእንጦጦ አካባቢ የወንዝ ዳርቻ የተበከለ ከመሆኑ ባሻገር ምሽት ብቻ ሳይሆን በቀንም ለመንቀሳቀስ የሚያስፈራ ነበር፡፡ አሁን ውብና ፅዱ፣ ሰዎች የሚዝናኑበት፣ የልማት ስፍራ ሆኗል። ቦታውን ለአትክልት እና ፍራፍሬ ምርት ማምረቻ ዝግጁ ከማድረግ ጀምሮ እንጆሪው ተተክሎ ለምርት እስኪደርስ ላለፈው አንድ ዓመት የስራ ዕድል ተፈጥሮላት እየሰራች እንደምትገኝ ያነሳችው ወጣት አማረች፣ አሁን ላይ እንጆሪው ለምርት ደርሶ በማየቷ ደስተኛ ሆናለች፡፡

ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ያለው የመልሶ ማልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተመርቆ ከሰሞኑ ለህዝብ አገልግሎት በይፋ ክፍት ሆኗል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ “ልማቱ የተራቆቱ አካባቢዎችን በዘመናዊ የአፈር ጥበቃ እና በወንዝ ማጣራት ወደ አረንጓዴ ስፍራዎች በመቀየር፣ የፍራፍሬ ፓርኮችን፣ ከእግር ጉዞ እና ከብስክሌት መንገዶች ጋር በማቀናጀት መዲናችንን አድሷል” ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ ያለው አካባቢ ወደ ተፈጥሯዊ ይዘቱ ተመልሶ የአካባቢውን ማህበረሰብ አኩሪ የስራ ባህል የሚዘክሩ ሐውልቶችና ቅርሶች ተገንብተውለት ፍፁም ማራኪ እና የሚያስደንቅ ገፅታን ተላብሶ መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ 597 ሄክታር ቦታ እና 9 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን ለመዝናኛ፣ ለንግድና ለተለያዩ ማህበራዊ ኩነቶች ተስማሚ በሆነ መልኩ የተገነባ ሰፊ የከተማ መናፈሻ ሆኗል። በከተማ ግብርና ስራዎች 15 ሄክታር ቦታ በአረንጓዴ የተሸፈነ ሲሆን፣ ቀሪው ደግሞ በ210 ቀፎ ዘመናዊ ንብ እርባታ፣ በአበባ እና በእፅዋት ጋርደን ለምቷል። በተጨማሪም 6 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር የተሽከርካሪ መንገድ፣ 8 ኪሎ ሜትር የሳይክል መንገድ፣ 22 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ፣ 4 ኪሎ ሜትር የሃይኪንግ መንገድ፣ 39 የደለል መቆጣጠሪያ ግድብ (ቼክ ዳም) ተገንብተዋል። 2 አዲስ የተሽከርካሪ ድልድዮች፣ 3 ነባር የተሽከርካሪ ድልድዮች እድሳት ተደርጎላቸዋል። እንዲሁም ሌሎች የአረንጓዴ ልማቶች አካትቶ የተገነባ መሆኑን ነው ያብራሩት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በወንዝ ዳርቻው ከተከናወኑ አስደናቂ ስራዎች መካከል የእንጆሪ ፍራፍሬ ልማቱ አንዱ እንደሆነ አንስተዋል፡፡ እንጆሪ በአካባቢው እንዲለማ ሲደረግ ለሙከራ ሲሆን ዛሬ አፍርቶ ለመበላት ደርሷል። ፍራፍሬው በየሁለት ቀኑ የሚለቀም፣ ዋጋውም ውድ እንደመሆኑ እንጆሪን ማስፋፋት ቢቻል ለሀገር ውስጥና ውጭ ገበያ በማዋል ከፍተኛ ገቢ ማስገኘት እንደሚቻል የሚያመላክት ውጤት ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም እንደ ሎሚ፣ ብርቱካን እና የደጋ ቡና ያሉ አትክልቶችና ዕፅዋት እንዲሁም ንብ በማነብ የተለየ ጣዕም ያለው ማር ማምረት ተችሏል፡፡ ልማቱ በአካባቢ ያለውን ውሃ የከተማ እርሻን ለማሳለጥ፣ ምግብ ለማምረት፣ ለሀገር በቀል ዕፅዋት ልማት ለማዋል እድል ፈጥሯል፡፡ ባህር ዛፍ በተፈጥሮ ውሃ የሚመጥ እንደሆነ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ባህር ዛፉ እየተወገደ፣ ሀገር በቀል ዛፎች እየጨመሩ ሲመጡ በተራራው ብዙ ውሃ መያዝና ለታችኛው ተፋሰስም የሚለቀቀው ውሃ እየጨመረ ይሄዳል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ በበኩላቸው ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሰጡት ማብራሪያ፣ በከተማ ወንዞች ላይ ያለውን ችግር ከመሰረቱ ለመፍታት ከእንጦጦ ተራራ ስራዎች ተጀምረዋል፡፡ ተራራው ውሃን መያዝ እንዲችል የተጎሳቆለውን 438 ሄክታር ተራራ መልሶ እንዲለማ ተደርጓል፡፡ ለዚህም በአካባቢ ጥበቃ የተካኑትን የኮንሶ ማህበረሰብ በማምጣት እርከን በመስራት ውሃውን ማስቀረትና ወደ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ተችሏል፡፡

እንጦጦ ተራራ በሚለማበት ወቅት ሁለት እውነታዎች ተገልጠዋል። ስፍራው ለፍራፍሬና የንብ እርባታ ምቹ እንደሆነ ማወቅ ተችሏል ያሉት አቶ ጥላሁን፣ ለሙከራ በተወሰነ ቦታ በተሰራው የእንጆሪ ልማት ከፍተኛ ውጤት ማግኘት ተችሏል። ይህንንም በከተማዋ ዙሪያ ከሚገኙ አርሶ አደሮች ጋር በመቀናጀት ለማስፋት ታቅዷል። በፕሮጀክቱ በተጨማሪም በርካታ በንብ ማነብ የተሰማሩ ማህበራት ገብተው እየሰሩ ሲሆን፤ ይህም እንደ ሀገር የተቀመጡ የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብሮችን በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ አስችሏል፡፡

የእንጦጦ ቀጨኔ የወንዝ ዳርቻ ልማት በውስጡ ያቀፋቸው ልማቶችና የሚያስገኛቸው በረከቶች እንዲሁ በአጭሩ ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡ በልማቱ ወንዙን ወደ ተፈጥሯዊ ይዘቱ ከመመለስ ባሻገር የመዝናኛ ስፍራ፣ የቱሪስት መዳረሻ በመሆን፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ የከተማዋን የውሃ አቅርቦት ዘላቂነት በማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ያለው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ ነው።

## ወቅታዊ ... ከገጽ 8 የዞረ

ኀዘን ይገልጻሉ።

እነዚህ ጥቃቶች የሀገሪቱን ብሔራዊ ዕድገት ለማደናቀፍ ከሚሹ አካላት፣ በአማራ ክልል ከሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥ አማፂ ቡድኖች እና ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ጥላቻ ካላቸው የውጭ ኃይሎች ጋር በጥምረት የተከናወኑ ሲሆኑ፤ ዓላማቸውም በኢትዮጵያ አለመረጋጋትንና የምርጫ መስተጓጎልን ለመፍጠር ሲደረግ የነበረ የጥፋት ውጥን ተከታይ ነው። መንግሥት 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ያለ አንዳች የፀጥታ ችግር ፍትሐዊና አሳታፊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ከአንድ ዓመት በላይ የዘለቀ ልዩ ትኩረትና ዝግጅት በማድረግ በቁርጠኝነት ሲሠራ ቆይቷል። በሌላ በኩል የጥፋት ኃይሎች ከባዕዳን ጋር ‘ፅምዶ’ የሚል ቁርኝት በመፍጠር ዕኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት ሰፊ የጥፋት ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል፣ ሀገራዊ ምርጫው እንዳይከናወን ሰፊ ርብርብ አድርገዋል። በተጨባጭም በቅድመ ምርጫ እና በምርጫ ወቅት የዜጎችን የመምረጥ መብትና ነጻነት ለመጋፋትና ለማደናቀፍ አለን የሚሉትን የጥፋት እጅ ዘርግተዋል።

እነዚህ የጠላት ኃይሎች በመደጋገፍና በመናበብ ዐመፅና ሁከት ለማነሳሳት፣ ከተሞችን በሽብር ጥቃት ለማወክ፣ በመንገዶች የደፈጣ ጥቃት በመፈጸም እንቅስቃሴ ለመገደብ እና በተወሰኑ አካባቢዎች ዒላማ አድርገው ነጥሎ ለማጥቃት ተንቀሳቅሰዋል። እንደ ማሳያ የጦር መሣሪያ፣ ተተኳሾችንና ሌሎች ሎጀስቲክሶችን በድጋፍ በማቅረብ በደቡባዊ ትግራይ በሚገኙ አዋሳኝ የአማራ ክልል አንዳንድ ቦታዎች ላይ ትንኮሳ ፈጽመዋል፤ በአማራ ክልል ባሕር ዳር፣ ጎንደር፣ ደብረ ብርሃን እና ወልድያ ከተሞችን ጨምሮ በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች እና ሲቪሎች ላይ ዒላማ በማድረግ ያካሄደው የሽብር እንቅስቃሴና ዝግጅት፣ በአዲስ አበባ ከተማ ባደራጃቸው የኅቡዕ ሴሎች አማካኝነት በተመረጡ አከባቢዎች ላይ ጥቃት እንዲፈጸም ተንቀሳቅሰው የነበረ ቢሆንም ይህን የጥፋት ሴራ እና ድርጊት እንዲከሽፍ ማድረግ ተችሏል።

በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል የሸኔ ሽብር ቡድን ከጽንፈኛው ፋኖ ታጣቂ ቡድን ጋር በመናበብ በአንዳንድ አካባቢዎች መንገዶችን በመዝጋት እንቅስቃሴ ለማስቆምና ለማስተጓጎል ፍላጎት የተንቀሳቀሰ ቢሆንም በጸጥታ ኃይሉ በተወሰደበት የተጠናከረ እርምጃ ፍላጎቱን ማሳካት አልቻለም። ቡድኑ በፀጥታ ኃይሉ የተወሰደበትን ርምጃ መቋቋም ባለመቻሉ እና ፍላጎቱን ማሳካት ባለመቻሉ ስስ ዒላማዎች ላይ ያተኮረ ርምጃ በመውሰድ የሃይማኖት እና የብሔር ግጭት ለመቀስቀስ በማለም በአርሲ ዞን አሰኮ እና አካባቢው ጥቃት በመፈጸም ሁሉን አይነት የጥፋት ርብርብ ያደረገ ቢሆንም ሁኔታውን በመቆጣጠር ፀጥታ ኃይላችን በእነዚህ ኃይሎች ላይ የተቀናጀ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል።

መንግሥት መሰል ሥጋቶችን በንቃት በመከታተል ላይ ሲሆን፣ በምርጫው ወቅትም በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተቀነባበሩ ተመሳሳይ ዕቅዶችን በስኬት ማክሸፍ ችሏል። በንጹሐን ዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን፤ ፍርሃትና ክፍፍልን ከሚያጎሉ የሚዲያ ዘመቻዎች ጋር በማስተሣሠር የተቀነባበረው ይህ እኩይ ተግባር፣ በመንግሥት የደኅንነት መዋቅርና ኦፕሬሽኖች አማካኝነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲስተጓጎል ተደርጓል። ብሔራዊ እና ኃይማኖታዊ ክፍፍልን ለመዝራት የኃይል ጥቃትን እና ውድመትን እንደ መሣሪያ የሚጠቀሙ አካላት በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ በግልጽ ሊወገዙ ይገባል። መሰል ተግባሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት የወደፊት ዕድል እንደሌላቸው ለማሳየት የተቀናጀ ብሔራዊ ምላሽ በመስጠት ወሳኝ እርምጃዎችን ይቀጥላል።

በንጹሐን ዜጎች ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ አካላት፣ ድርጊታቸውን ምክንያታዊ ለማስመሰል ምንም ዓይነት የፖለቲካ ንግግር ቢጠቀሙ፤ ወሳኝ ዓላማን እያሳኩ ሳይሆን ወንጀል እየፈጸሙ ነው። የፖለቲካ ቅሬታዎች በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ በብሔራዊ ምክክር ሂደት እና በዴሞክራሲያዊ ተቋማት አማካኝነት መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉ እና ሊያገኙ የሚገባቸው ናቸው።

## ከተፈጥሮ... ከገጽ 11 የዞረ

ዕድገታችን፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የከተማ እድሳት በተግባር የታየበት ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ይህን የመሰለው ሥራ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎችም በስፋት እየተተገበረ ይገኛል። ከበርካታ የሀገራችን ከተሞች በተጨማሪ እንደ ወንጪ፣ ጎርጎራና ሃላላ ኬላን ጨምሮ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በቅርብ ዓመታት የተሠሩ የተፈጥሮ መዳረሻዎች፣ የኢኮ-ቱሪዝምን እሴት ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ አድርገውታል። እነዚህ ስፍራዎች ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መሆናቸው፣ ኢትዮጵያ በቱሪዝም እና በመዝናኛ መዳረሻ ዘርፍ አዲስ ምዕራፍ እየከፈተች መሆኗን በግልጽ ያሳያል።

የዘርሲ ኢትዮጵያ ቱር ኤንድ ትራቭል መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ አቶ ወንድይፍራው ግርማ በበኩላቸው በአዲስ አበባ እና በሀገራችን የተሠሩ አዳዲስ መዳረሻዎች ለቱሪዝም ዕድገቱ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም እንጦጦ ፓርክን ጨምሮ በተለያዩ የመዲናዋ ክፍሎች የሚገኙትን የኮሪደር ልማቶች ለማስተዋወቅ የከተማ “Walking tourism” በሚል እየሠራን ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም በእነዚህ ቦታዎች አማካኝነት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት አዲስ በር ተከፍቷል። የቱሪዝም ፍሰቱን ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በማሰራጨት፣ ለነዋሪዎች አዲስ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። ይህም ልማቱ የከተማና የገጠርን የኢኮኖሚ ትስስር በማጠናከር፣ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚኖረው ፋይዳም የጎላ ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት እያሳየች ያለችው ተነሳሽነት ለሌሎች አገራት ጉልህ አርአያነት አለው። በተለይም በከተሞች ውስጥ እየተከናወኑ ያሉት የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶችና የአረንጓዴ መናፈሻዎች፣ የተፈጥሮን ውበት ከዘመናዊ የከተማ ፕላን ጋር በማቀናጀት ረገድ የላቀ ብቃት እያሳዩ ነው። ይህ ስኬታማ እንቅስቃሴ፣ ሌሎች ታዳጊ አገራት በአካባቢ ጥበቃና በከተማ ልማት እንዲሁም በመዝናኛ መዳረሻዎች መካከል ሚዛን መፍጠር እንደሚችሉ በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል።

መዝናኛን ከአረንጓዴነት ጋር ማዋሃድ የዜጎችን አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጤና ከመጠበቅ ባለፈ፣ የሀገሪቱን ገጽታ በእጅጉ ቀይሮታል። በየከተሞቹ የሚታዩት ለምለም መናፈሻዎች ሰዎች ከግርግር ወጥተው አእምሯቸውን የሚያሳርፉባቸው፣ ለአካላዊ እንቅስቃሴ የሚጠቀሙባቸውና ንጹሕ አየር የሚተነፍሱባቸው የጤና ማዕከላት ሆነዋል። ይህ የለውጥ ሥራ የከተሞችን ገጽታ ወደ ሕያውና አረንጓዴ የኑሮ ስፍራ በመቀየር፣ የዜጎችን የኑሮ ጥራት ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡

በአጠቃላይ ከአካባቢ ጥበቃና ከተፈጥሮ ጋር የተወዳጁ በአዲስ አበባ የሚገኙ ዘመናዊ መናፈሻዎችም ሆኑ እንደ ወንጪ፣ ጎርጎራና ሃላላ ኬላ ያሉ የተፈጥሮ መዳረሻዎች፣ ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን አቅም በግልጽ እያሳዩ ነው። ይህ አረንጓዴ አብዮት ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን በማረጋገጥ፣ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ የቱሪዝምና የመዝናኛ ካርታ ላይ የላቀ ቦታ እንዲኖራት የሚያደርግ ነው፡፡

አመልካች ዝናሽ ሀይሉ እና ቢታንያ ዘሪሁን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 በካርታ ቁጥር 015973 በሴሪ ቁጥር 107157 በ ዘሪሁን ኬርጋ ወልደጊዮርጊስ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ/9785/07 ሴሪ ቁጥር 089471 በአቶ አበራ ሀይሉ ይህደጎ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚንየም ሱቅ ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ተደራጅቶ በመመሪያ መሰረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች አቶ ያሬድ ገደቦ ወንበራ ካርታ ስለመጥፋቱ ቦሌ ክ/ከተማ ይዞታ አገልግሎት በደብዳቤ ቁጥር ቦ/ክ/ከ/ይዞ/አስ/የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ጽ/ቤት 135530/2011 በቀን 02/11/2011 ዓ/ም ለጋዜጣ እና ለማስታወቂያ የተጻፈ ቢሆንም ሲጻፍ የካርታ ቁጥር ስህተት በመሆኑ በድጋሚ ተስተካክሉ እንዲጻፍ በአመለከቱት መሰረት አቶ ያሬድ ግደቦ ወንበራ የጋራ ህንፃው የሚገኝበት ቦታ ስም ቦሌ አራብሳ የካርታ ቁጥር ቦ/አራ/11/82/4/4/12599/128010/01 ሴሪ ቁጥር 1511600 በቀድሞ ወረዳ 11 ብሎክ B-368 የህንጻ ቁጥር B-368 የወለል ቁጥር 1ኛ ፎቅ የቤት ቁጥር B-368/11 የቤቱ ስፋት 37.16 የቤቱ አገልግሎት መኖሪያ የሚገኘውን ይዞታ ሰነድ የሚገልጽ ኦርጅናል ካርታ ስለጠፋ አገልግሎት ለመስጠት ካርታው መምከን ስላለበት ለአሰራር እንዲያመቸን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞ እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ፅ/ቤት በወረዳ 12 ገብረዩሃንስ በርሄ ወልደጊዮርጊስ ስም የተመዘገበ ይዞታ የቤቱ ልዩ መለያ ቁጥር AA000051207436558040l8 የተሰጠበት ቀን 02/13/2013 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር 1599/18 በቀን 06/09/2018 ዓ.ም የሚገልፅ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለሁ ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ፅ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቶ ብርሃን ተስፋው ኃይሌ ስም የተመዘገበ ይዞታ ወረዳ 07 የይዞታ መለያ AA000090712077 የሆነ ካርታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን 20/09/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ገበያነሽ ደገፉ ካሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA000061007258191000 7 ሴሪ ቁጥሩ C 155327 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች አንዱአለም ደበሌ አረዳ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 በካርታ AA000070805496 በሴሪ ቁጥር 0126252 በ አንዱአለም ደበሌ አረዳ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወርቅነሽ ታምሩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ቦሌ/12/71/8/19/129083/00 በሴሪ ቁጥር 1527527 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ፍቅርተ ሀይለእየሱስ ገበየሁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ክልል ውስጥ የሚገኝ የኮንደሚኒየም ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 056676 የሴሪ ቁጥር 01441978 የቤቱ ስፋት 132.07 ካ.ሜ ለመኖሪያ የሚያገለግል የሆነ በስማቸው የተደራጀ ማህደር በማይታወቅ ሁኔታ ከጽ/ቤታችን የጠፋባቸው በመሆኑ ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማኛውም ምክንያት የጠፋውን ማህደር ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ማህደር አደራጅተን የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ሳሙኤል በላቸው በቀለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር AA00006050254201107006 የሆነ የጋራ መኖሪያ ቤት በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

## የሙስሊም ስጋ ቤት ኪራይ ጨረታ

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው ማህበራችን ደራሽ ለመርካቶ ኃላ/የተ/ሁ/ ሽ/ህ/ስ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በስሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ውስጥ የተለያዩ ቦታ የሚገኙ 2 ቤቶችን ለሙስሊም ስጋ ቤት አገልግሎት ብቻ ማከራየት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ቤቱን ተከራይቶ ለህብረተሰቡ አንድ ኪሎ በ520 ብር ለመሸጥ የሚስማማ ተከራይ ብቻ በጨረታው መሳተፍ የሚችል ሲሆን ቤቶቹም

1. በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቀድሞ ቀበሌ 10 ሻወል ደማ ት/ቤት አካባቢ የሚገኝ
2. በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቀድሞ ቀበሌ 06 ውስጥ የሚገኝ መሆኑን አውቃችሁ ከላይ በተዘረዘረው መሰረት ለመስራት የሚስማማ ተጫራች የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ለመገኘት እና ቤቶችን በአካል በመገኘት በመመልከት ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 ተከታታይ የስራ ቀናት የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 200 በመክፈል በመግዛት የሚከራዩበትን ዋጋ በመጥቀስ በስም በታሸገ ኢቨሎፕ በማድረግ ለዚህ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ላይ በማስገባት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ማህበሩ በጨረታው የተሻለ ዘዴ ከአገኘ በጨረታው አይገደድም

**አድራሻ፡-** በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የቀድሞ ቀበሌ 04 ከአውቶቡስ ተራ ወደ 7ኛ በሚወስደው መንገድ አጋማሽ ላይ የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ይገኛል፡፡

ስልክ ቁጥር 0112 73-35-91

**ደራሽ ለመርካቶ ኃላ/የተ/ሁ/ ሽ/ህ/ስ/ማህበር**

---

## የጨረታ ማስታወቂያ

ድርጅታችን እነሆ ፍቅር የበጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት በበጎ አድራጎትና በግብረ ሰናይ ስራ ላይ የተሰማራ ሲሆን የ2018 በጀት አመት አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴን ኦዲት ለማስደረግ በዘርፉ (በሙያው) ብቃት ባላቸው ህጋዊ ድርጅቶች ስራውን ማሰራት ስለሚፈልግ በዚሁ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በሀገር አቀፍ ግልፅ ጨረታ በማውጣት አወዳድሮ አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ጋር ውል በማሰር አገልግሎቱን መግዛት ይፈልጋል።

**በዚህም መሰረት**

1. በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው።
2. በተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል።
3. ንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል።
4. የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት በኃላ በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚያው ዕለት4፡30 በግለፅ ይከፈታል። 11ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይከፈታል።
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ከአትላስ ወደ ሃያ ሁለት በሚወስደው መንገድ አትላስ ሆቴል ከፍ ብሎ ዮሊ ሆቴል ፊት ለፊት ባቦ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 በሚገኘው ቢሮዋችን በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል።
6. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለተጨማሪ ማስረጃ** ስ.ቁ 0911227544/ 0946725884


**እነሆ ፍቅር የበጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት**

# የአረንጓዴው ልማት ስፖርታዊ ገጽታ

**በሳህሉ ብርሃኑ**









ፎቶ- ከገፀ ድር

ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድሐኒዓለም በተሰራው የወንዝ ዳርቻ ልማት የ'እግር ቴኒስ'ን ጨምሮ በርካታ የስፖርታዊ እንቅስቃሴ መከወኛ ስፍራዎች ተዘጋጅተዋል

የቴክሳስ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ቲና ማሪ ዋሊሴክ በፈረንጆቹ 2010 The Relationship between Levels of Greenery and Landscaping at Track and Field Sites በሚል ርዕስ ያሳተሙት ጥናት አስገራሚ እውነታን ይነግረናል። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአረንጓዴነት እና ምቹ የአየር ንብረት በአትሌቲክስ ውጤት፣ በአትሌቶች ግንዛቤ እና በውድድር ጭንቀት ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመርመር ነበር። ከ200 በላይ አትሌቶችን አካትቶ በተሰራው ጥናት መሰረት፣ እፅዋትና አረንጓዴ አካባቢዎች ላይ መሰልጠንና መወዳደር ጭንቀትን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚቀንስ እና ውጤትን እንደሚያሻሽል ያስረዳል።

በተቃራኒው አብዛኞቹ የአትሌቶች መጥፎ የአፈፃፀም ምልክቶች የሚታዩት ዝቅተኛ የአረንጓዴ ደረጃ ባላቸው ስፍራዎች ሲሰለጥኑና ሲወዳደሩ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። ምርጥ የአፈጻጸም ውጤቶችን ያመጡ አትሌቶች ግን አረንጓዴያማ እና የተስተካከለ የአየር ንብረት ባለበት የትራክ እና የሜዳ ቦታ በመሰልጠናቸው እንደሆነ ያትታል። ከፍተኛ የስፖርት ባለሙያው አቶ በኃይሉ በቀለ እንደሚያስረዱትም፣ ስፖርተኞች ለውድድር ሲዘጋጁ ከአካልና አዕምሮ ስልጠና፣ ከተገቢ አመጋገብና ማገገም ጎን ለጎን የሚሰልጥኑበትና የሚወዳደሩበት አካባቢ የሙቀት መጠን እና የአየር ብክለት ጉዳይም እጅግ አሳሳቢና ወሳኝ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት የሰፈራ ፕሮግራም (UN-Habitat) በ2020 ባወጣው ሪፖርት፣ የከተማ ጽዳት ለነዋሪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ ያለውን ወሳኝነት በስፋት ያትታል። ጽዱ ከተሞች ለስፖርት ምቹ በመሆናቸው ምክንያት በነዋሪዎቻቸው ላይ የሚታየውን የሕክምና ወጪ በከፍተኛ መጠን እንደሚቀንሱ ሪፖርቱ ያስረዳል። ጥናቶች እንደሚያሳዩትም በአማካይ 10 ሺህ እርምጃዎችን አልያም ቢያንስ 8 ኪሎ ሜትር ገደማ የሚሆን ርቀትን በየዕለቱ መጓዝ የልብን ጤንነት ለማሻሻል፣ የደም ዝውውርን ለማሳለጥ፣ የአእምሮ ውጥረትን ለመቀነስ፣ እንደ ስኳርና የደም ግፊት ያሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ትልቅ አቅም አለው። በተቃራኒው እንደ ዓለም አካባቢ ጥበቃ ድርጅት መረጃ ከሆነ፣ በአንድ ሺህ ከተሞች ውስጥ ብቻ 43 ሺህ ሰዎች የሚሞቱት በአረንጓዴ ቦታዎች እጦት ምክንያት ሲሆን፣ በእነዚሁ ከተሞች 25 በመቶ ሰዎች ከአረንጓዴ ስፍራ እጦት የተነሳ ከስፖርት ውጪ ይሆናሉ።

የአዲስ አበባን የመንገድ ገጽታ ስር ነቀል በሆነ መልኩ የቀየሩ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች፣ ለስፖርት አፍቃሪዎች ትልቅ የምስራች ይዘው መጥተዋል። እንደ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ በእንጦጦ እና በጉለሌ አካባቢዎች የተከናወነው የመልሶ ማልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክትና ሌሎች የኮሪደር ልማት ውጤቶች ለነዋሪው ክፍት የሆኑና ለስፖርት የሚጋብዙ ስፍራዎችን አበርክተዋል። የወዳጅነት አደባባይ ሰፊ ክፍት ቦታዎች ያሉት በመሆኑ፣ በቡድን የሚሰሩ እንደ ዮጋ፣ ኤሮቢክስ እና የጠዋት ሩጫዎችን ለማከናወን ምቹ ሆኖ ተገንብቷል።

በቀጨኔ መድኃኔዓለም፣ በእንጦጦ እና በጉለሌ አካባቢዎች የተከናወነው የመልሶ ማልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማትም የስፖርቱን ዘርፍ ያልዘነጋው ሌላኛው ልማት ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ የእንጦጦ ተራራማ ስፍራ የስፖርትና የጤናማ ህይወት መፍለቂየ ነው። የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በተለይ ለሩጫ፣ ለፈጣን እርምጃ (Hiking) እና ለሳይክል ስፖርት እጅግ ተመራጭ ያደርገዋል። ረዣዥም ዛፎች የፀሐይን ትኩሳት በመጋረድ ለስፖርተኞች ምቹ ጥላ የሚፈጥሩ ሲሆን፣ የኮረብታው አቀበትና ቁልቁለት ደግሞ የሰውነትን ጥንካሬ እና የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ ተወዳዳሪ የሌለው የተፈጥሮ ማሰልጠኛ ስፍራ ሆኖ ያገለግላል።

በቅርብ ዓመታት የተገነባው ዘመናዊው የእንጦጦ ፓርክ ለአካባቢው ስፖርታዊ እንቅስቃሴ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ፓርኩ ለየት ያሉ ስፖርቶችን ለሚወድዱ ሰዎች ምቹ የሳይክል መጋለቢያ መንገዶችን፣ በአየር ላይ የመንጠልጠል ጀብዱ እና በደን ውስጥ የሚደረጉ የሰውነት ማጎልመሻ ስፍራዎችን አዘጋጅቷል። ይህ ደግሞ ፕሮፌሽናል ስፖርተኞችን ብቻ ሳይሆን፣ ቅዳሜና እሁድን ከቤተሰብ ጋር በስፖርትና በመዝናናት ለማሳለፍ ለሚፈልጉ የከተማዋ ነዋሪዎች ተመራጭ ማረፊያ አድርጎታል።

የእንጦጦ ስፖርታዊ ማራኪነት ይበልጥ ደምቆ የተገነባው በቀጨኔ መድኃኔዓለም፣ በእንጦጦ እና በጉለሌ አካባቢዎች ተጠናቆ ሰሞኑን ለአገልግሎት ክፍት የተደረገው ታላቅ የመልሶ ማልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት የአካባቢውን የተፈጥሮ ውበት ይዞታ ከማሳደጉም በላይ፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል። በዚህ የወንዝ ዳርቻ ልማት ውስጥ የተካተቱት ውብ የእግር ጉዞ እና የሳይክል መጋለቢያ መንገዶች፣ ዘመናዊ የሜዳ ላይ የአካል ብቃት ማጎልመሻ ስፍራዎች እና ለተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የተዘጋጁ ሜዳዎች ለአካባቢው ነዋሪዎችና ለስፖርት አፍቃሪያን አዲስ የመነቃቃት መንፈስ ይዘው መጥተዋል። ከተራራው የሚወርደውን ንጹህ አየር እና የለመለመውን የወንዝ ዳርቻ ተፈጥሮ እየተነፈሱ ስፖርት መስራት መቻሉ፣ እንጦጦንና አካባቢውን ወደር የለሽ የስፖርተኞች እና የጤናማ ህይወት ማዕከል አድርጓታል።

ይህንን ታላቅ የልማት ፕሮጀክት መርቀው ለአገልግሎት ክፍት ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለአካባቢው ስፖርታዊ ምቹነትና ለነዋሪው ጤና ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ በጉልህ አንስተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት አስተያየት፤ አካባቢው የተፈጥሮ ውበቱና ንጹህ አየሩ ተጠብቆ፣ ዘመናዊ የስፖርት መሠረተ ልማቶች እንዲካተቱበት የተደረገው ማህበረሰቡ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን የዕለት ተዕለት ህይወቱ አካል እንዲያደርግ ታስቦ መሆኑን ገልጸዋል።

አክለውም፣ ነዋሪዎች የተገነቡትን ውብ የሳይክል፣ የእግር ጉዞ መስመሮች እና የሜዳ ላይ ስፖርት ማዘውተሪያዎችን በስፋት እንዲጠቀሙባቸው ጥሪ አቅርበዋል። ይህ ፕሮጀክት ከተማን ከማስዋብ ባለፈ፣ ማህበረሰቡ በነፃነትና በሰላማዊ አካባቢ ስፖርት እየሰራ ጤናማ ትውልድ እንዲገነባ ታላቅ ዕድል የፈጠረ መሆኑን በአጽንኦት አመልክተዋል።

በእነዚህ አረንጓዴ ስፍራዎችና መጫወቻ ሜዳዎች ላይ ሊዘወተሩ ከሚችሉ አዳዲስ ስፖርቶች መካከል አንዱ የ'እግር ቴኒስ' ነው። ኳስን መሬት ሳያስነኩ በአየር ላይ ማቆየት የብዙ እግር ኳስ አፍቃሪያን የልጅነት ትዝታ ቢሆንም፣ አሁን ግን ይህ ጨዋታ መልክና ህግ ይዞ፣ የቴኒስን መረብ እና የእግር ኳስን አስደናቂ ክህሎት አዋህዶ የ'እግር ቴኒስ' በሚል ስም ዓለምን እያስገረመ ይገኛል። ይህ ስፖርት ፍጥነትን፣ ትኩረትን እና የመተጣጠፍ ብቃትን በአንድ ላይ የሚጠይቅ አዲሱ የሜዳ ላይ ጥበብ ነው።

ይህ ስፖርት እ.ኤ.አ. በ1922 በቀድሞዋ ቼኮዝሎቫኪያ (የአሁኗ ቼክ ሪፐብሊክ) ስላቪያ ፕራግ (Slavia Prague) የእግር ኳስ ክለብ ወጣት ተጫዋቾች 'ኖፔሲራዶ' በሚል ስም ተጀመረ። እ.ኤ.አ በ1940ዎቹ የመጀመሪያው ይፋዊ ህግ የወጣለት ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ1987 ደግሞ በዓለም አቀፉ የእግር ቴኒስ ማህበር (ፊፋ) ተመስርቶ ጨዋታው ህጋዊ የዓለም አቀፍ ውድድር ለመሆን በቃ። ዛሬ ላይ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ስሎቫኪያ፣ ሮማኒያ እና ሀንጋሪ የጨዋታው ኃያላን ሲሆኑ፣ ደቡብ ኮሪያና የላቲን አሜሪካ ሀገራትም ፈጣን እድገት እያሳዩ ነው።

የ'እግር ቴኒስ' ከትርፍ ጊዜ መዝናኛነት አልፎ አሁን ላይ የራሱ ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን እና የዓለም ዋንጫ ያለው ትልቅ ስፖርት ሆኗል። ዛሬ ላይ የተገነቡት አዳዲስ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች ፓርኮችን በመጠቀም ይህንን ስፖርት ይበልጥ ቢዘወተር፣ የወጣቶችን የኳስ ክህሎት ከማሳደግ ባለፈ አዲስ የስፖርት አማራጭና ማራኪ መዝናኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ከእንጦጦ እስከ ቀጨኔ መድሐኒዓለም አካባቢ ባለው የወንዝ ዳርቻ ልማት የተካተቱት የስፖርት ማዘውተሪያዎች በየማለዳው በጭጋግ የተሸፈነውን የተራራ መንገድ ተከትለው የሚሮጡ ወጣቶች፣ የነገውን የዓለም ሻምፒዮናነት ህልም የሚጻፍባቸው ስፍራዎች ሆነዋል።

# ትዕይንተ ፎቶ



## “ከአዲስ አበባ እስከ በሻሻ ”

